




የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ


የ2017 በጀት ዓመት

የተደገፈ በጀት

(ጥራዝ I በጀት ማጠቃለያ)

ግንቦት 30/2016


ጠቅላላ ወጪ /በቢሊዮን ብር/
የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ, 14.0 , 1.4%
ክልል ድጋፍ, 222.7 , 22.9%
መደበኛ, 451.3 , 46.5%
ካፒታል , 283.2 , 29.2%


ጠቅላላ ገቢ /በቢሊዮን ብር/
የአገር ውስጥ ብድር 325.6 33.6%
የአገር ውስጥ ገቢ 563.6 58%
የውጭ አገር ብድር 32.9 3.4%
የውጭ አገር እርዳታ 49.1 5%

ማውጫ

1 መግቢያ 1
2 የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም (2013-2015) 3
3 ያለፉት ዓመታት የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም (2013-2015) 10
3.1 የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም 10
3.1.1 የመንግስት ገቢ አፈጻጸም 10
3.1.2 የመንግስት ወጪ አፈጻጸም 12
3.1.3 የበጀት ጉድለት እና የመንግስት ዕዳ ሁኔታ 14
3.1.4 የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር 16
4. የ2016 በጀት አፈጻጸም ዕይታ 19
4.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ አፈጻጸም የኢኮኖሚ ዕድገት 19
4.2 የ2016 በጀት የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም 20
5. የ2016 በጀት ዓመት ገቢ፣ ወጪና የወጪ አሸፋፈን 22
5.1 ኢኮኖሚያዊና ፊሲካል ታሳቢዎች 23
5.1.1 ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች 23
5.1.2 የፊሲካል ፖሊሲ ታሳቢዎች 24
5.2 የፌዴራል መንግሥት የገቢ ታሳቢዎች 25
5.2.1 ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች ታሳቢዎች 29
5.2.2 የውጭ ዕርዳታና ብድር (soft loan) ዋና ዋና ታሳቢዎች 29
5.3 የፌዴራል መንግስት ወጪ 30
5.3.1 የፌዴራል መንግስት መደበኛ ወጪ 31
5.3.2 የፌዴራል መንግስት ካፒታል ወጪ 31
5.3.3 የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ 32
5.3.4 የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ 32
6. የ2017 ፕሮግራም በጀት አዘገጃጀትና ድጋፍ 33
6.1. የ2017 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ዋና ዋና ታሳቢዎች 33
6.1.1. ጠቅላላ ታሳቢዎች 33
6.1.2. የመደበኛ ወጪ ታሳቢዎች 35
6.1.3. የካፒታል ወጪ ታሳቢዎች 36
6.2. ጠቅላላ በጀት 37
6.2.1 የመደበኛ ወጪ 39
6.2.2 የካፒታል ወጪ 44
6.2.3. ከፌዴራል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው 49
7. የወጪ አሸፋፈን 51

1 መግቢያ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት ዓመታት የገጠሙትን ተደራራቢ ተግዳሮቶች ተቋቁሞ በማገገም ላይ ሲሆን፤ በዓለማችን ከትከሰቱተ ቀውሶች አኳያ የበርካታ ሀገራት ኢኮኖሚ ዕድገት በእጅጉ የተዳከመ ቢሆንም፤ ሀገራችን ከሌሎች ሀገራት በተሻለ ሁኔታ ዕድገት ማስመዝገቧን ቀጥላለች፡፡ በቀጣይ ዓመታትም ይህ ዕድገት እንደሚቀጥል የዓለም ባንክ እና ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት ትንበያዎቻቸውን አስቀምጠዋል፡፡

በሌላም በኩል ሀገራችን በአለም አቀፍ ሁኔታ ካጋጠሟት ተግዳሮቶች በተጨማሪ በተፈጠረባት ዘርፈ-ብዙ ውስጣዊ ተግዳሮቶች የተነሳ የማክሮ-ኢኮኖሚውን መዛባት ለማስተካከል እና የኢኮኖሚ ዕድገቱን በሚፈለገው መጠን ለማስቀጠል የተያዙ ውጥኖች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፈጠሩ አልቀረም። ተግዳሮቶቹ፤ ኢኮኖሚው ላይ ባሳደሩት ጫና ምክንያት በታቀደው ልክ ገቢ እየተሰበሰበ ባለመሆኑና የሀገሪቱ የልማት አጋሮች የሚሰጡትን የቀጥታ በጀት ድጋፍ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ በማቋረጣቸው፤ የተከሰተውን ከፍተኛ የመንግስት የወጪ ፍላጎት ለመሸፈን እና የተከሰተውን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ለማስተካከል ተግዳሮት ገጥሟል፡፡ ይህም በዋናነት የመንግስትን የፊሲካል አቅም ከመፈታተኑም በላይ፤ የፊሲካል ተጋላጭነትን (Fiscal Vulnerebility) እንዲጨመር አድርጓል:: በመሆኑም ለተጀመሩ የልማት ሥራዎች የተያዘውን በጀት ቅድሚያ ማግኘት ያለባቸውን የመለየትና ቅድሚያ የመስጠት (reprioritization) እንዲሁም የዕዳ ክፍያን የማሸጋሸግ እና እፎይታ የማግኘት እርምጃዎች እየተወሰዱ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም እረገድ የሀገር ውስጥ ብድር ክምችት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፤ በቀጣይ ዓመታትም የብድር ክፍያ ፍላጎቱ በከፍተኛ መጠን እንደሚጨምርና የፊሲካል ጫና እንደሚያስከትል ስለሚጠበቅ ጥንቃቄ የተሞላው የፊሲካል ፖሊሲ (fiscal prudence) መከተል የግድ ይላል፡፡ በተጨማሪም መንግስት ይህንን የአገር ውስጥ የብድር ክፍያ ፍላጎት በወቅቱ ባለማስተናገዱ በአበዳሪ ተቋማት የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ላይ የሚኖረው ጫና ለፋይናንስ ዘርፉ እና ለኢኮኖሚው ስጋቶችን እንደሚፈጥር እሙን ነው፡፡

መንግስት የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አንድን በመተግበር ተፈጥረው የነበሩ ተግዳሮቶችን ተጽእኖ ማለዘብ ባይችል ኖሮ ሊከሰት ይችል የነበረውን ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ መግመት አያዳግትም። ከተግዳሮቶቹ፤ መደራረብ የተነሳ አሁንም እንደ የዋጋ ግሽበት፣ የብድር ጫና፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ የስራ አጥነት የመሳሰሉ

ችግሮችን ሙሉ በሙሉ መቅረፍ ሳይቻል ቀርቷል። በቀጣይም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ መልሶ ግንባታ ለማፋጠን፣ ያለፉትን ዓመታት የኢኮኖሚ ሪፎርም ስኬቶችን ለማጠናከር፣ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ለማረም፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ለማስቻል፣ አዲስ የዕድገት እድሎችን ለመክፈት፤ ሁለተኛዉ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ከተያዘው በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ መደረግ ጀምሯል። ይህ የማሻሻያ ፕሮግራም የተመቻቸ የመዋዕለ ንዋይ እና ንግድ ከባቢን መፍጠርን፣ የማክሮ-ኢኮኖሚ መርረጋጋት መፍጠርን፣ በተመረጡ ዘርፎች የምርታማነትን ማሳደግን እና አቅም ያለው እና ውጤታማ የሲቪል ሰርቪስ ሀይል መገንባትን እንደዋና ምሰሶ አድርጎ የተቀረጸ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የማሻሻያ ፕሮግራሙ ቁልፍ አገራዊ እቅዶችን በማመሳከር የተቀረጸ ሲሆን፣ የዓስር አመቱን የብሔራዊ የልማት ዕቅድ ከማሳካት አንጻር ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል። ለዚህም መሻሻያ ስኬት ጠንክሮ ከመስራት ባለፈ ሊያመጣቸው ሚችለውን ስኬቶች በማጤን በየዘርፉ ርብርብ እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ተገቢ ነው።

በተጨማሪም የ2017 በጀት ዝግጅትም ከዚሁ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሁለት ጋር ተጣጥሞ እና የገጠመንን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት፤ በተለይም ደግሞ ለብድር ክፍያ ጫናው የተለየ ትኩረት በመስጠት የተዘጋጀ ነው። በአጠቃላይ፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደተከተልነው ዋናው የትኩረት አቅጣጫ ጥብቅ የገንዘብ እና ፊሲካል ፖሊሲ (fiscal consolidation and monetary restraint) በመተግበር የተከሰተውን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ማስተካከልና መረጋጋትን መፍጠር መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

ይህ ሰነድ በቅድሚያ ያለፉት ሶስት ዓመታት የአጠቃላይ ኢኮኖሚና የፊሲካል ፖሊሲ አፈፃፀምን በአጭሩ በመዳሰስ ይጀምራል። በመቀጠልም የኢኮኖሚና የፊሲካል ፖሊሲ አቅጣጫዎች የዳሰሰ ሲሆን፣ ቀጥሎም የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ የዘጠኝ ወራት የኢኮኖሚና ፊሲካል አፈጻጸም በአጭሩ ከቀረበ በኋላ በመጨረሻም የ2017 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ዝርዝር የገቢ፣ የወጪና የወጪ አሸፋፈን ዕቅድ ከትንታኔ ጋር ቀርቧል፡

2 የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም (2013-2015)

መንግስት ባለፉት አመታት ተግባራዊ ያደረጋቸው መጠነ ሰፊ የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ኢኮኖሚው የገጠሙትን ተደራራቢ ተግዳሮቶችና ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም እንዲችል (resilience building) ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በመሆኑም ኢኮኖሚዉ በተለይ ከ2012-2014 ባሉት ዓመታት የገጠሙትን ተግዳሮቶች ተቋቁሞ በማንሰራራት ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ የኢኮኖሚው አፈጻጸም ሲታይ አገሪቷ የገጠሟትን ተግዳሮቶች ከግምት ማስገባት አስፈላጊ ነው። ከነዚህ ተግዳሮቶች ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፤ የአበዳሪዎች እና የለጋሾች እጅ መሰብሰብ (funding squeeze)፣ ነዳጅን ጨምሮ የተላያዩ ሸቀጦች አለም አቀፍ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ማሻቀብ፤ ከዚህም ተያይዞ የውጭ ምንዛሬ ክምችት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣ የሃገር ውስጥ የዋጋ ንረት በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር፣ የዕዳ ክፍያ ጫና መፈጠር የመሳሰሉት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከተፈታተኑ ተግዳሮቶች መካከል ይገኙበታል። ከሌሎች ሃገሮች በተለየ ሁኔታ አገራችንን ከገጠሟት ተግዳሮቶች መካከል ጎልቶ ሊጠቀስ የሚችለው በተለያዩ የሃገሪቷ ክፍሎች የተከሰቱ ግጭቶች፣ ድርቅ እና ከነዚህ ጋር ተያይዘው የመጡ ተጽዕኖዎች ይጠቃሳሉ። ምንም እንኳን መንግስት በትግራይ ክልል ተከስቶ የነበረውን ግጭት በሰላማዊ መንገድ መፍታት ቢችልም፣ በአገራችን በተለየዩ አከባቢዎች ተመሳሳይ ግጭቶች መከሰታቸዉ በልማት ሥራዎቻችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደሩ ይገኛል። ኢኮኖሚው እነዚህን ተግዳሮቶች መቋቋሙ እሙን ቢሆንም፤ እያንዳንዱ ተግዳሮት ጥሎ ያለፈው ጉዳት ቀላል አይደለም። እነዚህ ተግዳሮቶች መንግስት ያቀዳቸውን እና በመተግበር ላይ ያሉትን የሪፎርም ስራዎች በማደናቀፍ፣ በማጓተት፣ በመቀልበስ፣ እንዲሁም የፊስካል ኮንሶሊዴሽን እና የሞኒታሪ ሪስትሬንት በተሻለ ሁኔታ እንዳይተገበር እንቅፋት በመሆን፣ የመንግስትን ገቢን በመቀነስ እና ወጪውን በመጨመር፣ የልማት ግኝቶችን ወደኋላ በመጎተት ያሳደሩት አለታዊ ትጽዕኖ ቀላል አይደለም።

በሌላ በኩል ባለፉት ሦስት አመታት ሀገሪቱ ላጋጠማት ዘርፈ-ብዙ ፈተናዎች እልባት ከመስጠት ጎን ለጎን ወሳኝ የሆኑ በዘላቂነት አይበገሬ የኢኮኖሚ ልማት ለመገንባት መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ ተግባራቶች ተከናውነዋል። ከነዚህም መካከል የአረንጓዴ አሻራ፣ የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር፣ እንዲሁም የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና ስርዓተ ምግብን ማሻሻል እንደዋነኛ ዓላማ በመውሰድ በመተግበር ላይ ይገኛል። በነዚህ ዓመታት ሲሰራበት የነበረው ምርትና

ምርታማነት ውጤት አፍርቶ፣ በስንዴ ምርት እራስን ከመቻል አልፎ ወደ ውጭ መላክ የተጀመረ ሲሆን፤ ይህም የውጭ ምንዛሬ ከማመንጨት በተጨማሪ በትጋት እና ቁርጠኝነት ከሰራን እንደሃገር ለውጥ ማምጣት የምንችል መሆናችንን ማሳያ ይሆናል፡፡ እነዚህ ጥረቶች በአጠቃላይ ምርት እና ምርታማነትን እና የስራ ዕድል ፈጠራን የሚያነለብት የኢኮኖሚ ሽግግር አጀንዳን ለማፋጠን ከፍተኛ ዕድል ይሰጣሉ ተብሎ ይታመናል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት ዓመታት የገጠሙትን ተደራራቢ ተግዳሮቶች ተቋቁሞ በ2015 በጀት አመትም የ7.2 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል። ይህ ዕድገት በቀደሙት ሶስት ዓመታት ከተመዘገበው የ 6.3 በመቶ የአማካይ የዕድገት ምጣኔ ወደ አንድ መቶኛ ነጥብ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን፤ ሌሎች አገሮች ካስመዘገቡት እድገትም ከፍ ያለ ነው። ለምሳሌ እንደ አለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ሪፖርት በተመሳሳይ ወቅት ከሰሃራ በታች ያሉ ሀጋራት በአማካይ የ3.3 በመቶ እድገት እንዳስመዘገቡ ተገምቷል። ምንም እንኳን ኢኮኖሚያችን በ2015 በጀት ዓመት በ7.5 በመቶ እንደሚያድግ ግብ ተቀምጦ የነበር ቢሆንም፤ በዓለም ዓቀፍ ደራጃ በተከሰተው ከፍተኛ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ፣ በሩሲያና ዩክሬን ጦርነት እንዲሁም የአለም የንግድ ሰንሰለት መዛባት እና የመሳሰሉት ምክንያቶች የዓለም ሀገራት ኢኮኖሚ ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ እያቀነሰ በለበት ሁኔታ ኢኮኖሚያችን ያስመዘገበው የእድገት ምጣኔ አመርቂ ነበር ማለት ይቻላል።

ይህም ኢኮኖሚያችን በሰሜኑ በሃገራችን ክፍል በተለይም በትግራይ ክልል ተከስቶ ከነበረው ግጭት መቆም ጋር ተያይዞ የመጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መነቃቃቶችን በማሳየት ላይ መሆኑን ያሳያል።

ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ (current market prices) **በ2013 በጀት አመት ከነበረበት ብር 4.3 ትሪሊዮን በ2015 በጀት አመት ከእጥፍ በላይ በማደግ ወደ ብር 8.7 ትሪሊዮን ከፍ ብሏል።** ከዚህም ጋር በተያያዘ የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት መረጃ እንደሚያመለክተው የዜጎች የነፍስ-ወከፍ ገቢ በ2013 በጀት በጀት ዓመት ከነበረበት 1,092 የአሜሪካ ዶላር በ2015 ወደ 1,549 የአሜሪካ ዶላር ከፍ ብሏል። ከላይ ከተጠቀሱት ተግዳሮቶች በተጨማሪ የገቢ አሰባሰቡ (resource mobilization) ሂደት አዝጋሚ መሆን፣ ከልማት አጋሮች እርዳታና ብድር ማግኘት አለመቻሉ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተፈጠረው የተጣበበ የመንግስት ፋይናንስ ሁኔታ

(fiscal space)፤ የመንግስት የልማት እንቅስቃሴዎች መገደብ ምክንያት የኢኮኖሚ ዕድገቱን በተፈለገው መጠን ማስኬድ ሳይቻል ቀርቷል።

የኢኮኖሚ ዕድገቱ ሰፊ መሰረት የነበረው ሲሆን ግብርና፣ የኢንደስትሪ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉ የራሳቸውን አስተዋጾ አበርክተዋል። በተለይም የኢንደስትሪ ዘርፉ ባለፈው ዓመት ካስመዘገበው ዝቅተኛ የዕድገት ምጣኔ በመውጣት የ2 መቶኛ ነጥብ ጭማሪ አስመዝግቧል። እንደሚታወቀው የኢንደስትሪ ዘርፉ በውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ በመንግስት ወጪ መቀነስ፣ አገሪቷ ከAGOA ከመታገዷ እንዲሁም አሁንም በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች ካሉ አለመረጋጋቶች በተያያዘ ዕድገቱ ውስን ሆኗል። ግብርናን በተመለከተ መንግስት በስንዴ ምርት እራስን የመቻል ፕሮግራም ነድፎ በመንቀሳቀሱ አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል። የኢንደስትሪ ዘርፉ የተሻለ እንቅስቃሴ በማሳየት በበጀት ዓመቱ በንጽጽር የተሻለ (7.7 በመቶ) የዕድገት ምጣኔ ያስመዘገበ ሲሆን ከጠቅላላ የሃገር ውስጥ ምርት ያለውንም ድርሻም አምና ከነበረው የ40 በመቶ ድርሻ ወደ 40.3 በመቶ አድጓል።

በሌላ መልኩ የተመዘገበው የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በአመዛኙ ከፍጆታ የመነጨ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህም እረገድ አጠቃላይ ፍጆታ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት አንጻር ያለው ድርሻ በ2012 በጀት አመት ከነበረበት የ81.1 በመቶ ድርሻ በ2015 ወደ 85.2 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። በሌላ ወገን የጠቅላላ ኢንቨስትመንት አፈጻጸም ባለፉት ሦስት ዓመታት የመቀዛቀዝ አዝማሚያ በመሳየቱ፤ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው የ35.3 በመቶ ድርሻ እየቀነሰ በመምጣት በ2015 በጀት አመት ወደ 22.2 በመቶ ደርሷል።

የዋጋ ንረቱ በ2015 በጀት ዓመት የተወሰነ መሻሻል ቢያሳይም፤ አሁንም ከ25 በመቶ በላይ በመሆን ለኢኮኖሚው አይነተኛ ተግዳሮት ሆኖ ቀጥሏል። የዋጋ ንረቱ በምግብ እና ምግብ ነክ ባልሆኑ ዕቃዎች የዋጋ መጨመር ምክንያት የመጣ ቢሆንም ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ በ2015 በጀት ዓመት ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ዋጋ ከፍተኛውን ድርሻ ወስዷል። የአጠቃላይ የዋጋ ግሽበቱ በ2013 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ከነበረበት የ 18.7 በመቶ ምጣኔ እየጨመረ በመምጣት በህዳር 2015 የ35.1 በመቶ ከፍተኛ ምጣኔ ደርሶ የነበረ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ቀጣይ ወራት መሻሻል በማሳየት በነሃሴ 2015 ወደ 28.2 በመቶ ዝቅ ሊል ችሏል። በ2013 የነበረው የአጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ በአማካይ 21.4 በመቶ የነበረ ሲሆን፤ በ2014 በጀት

ዓመት የ13.1 መቶኛ ነጥብ ጭማሪ አሳይቷል። መንግስት ከወሰዳቸው እርምጃዎች በተጨማሪ አንዳንዶቹ ተግዳሮቶች ተጽእኖ እየቀነሰ በመምጣቱ፤ በ2015 በጀት ዓመት የነበረው የአጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ በአማካኝ ወደ 31.9 ዝቅ ሊል ችሏል። አሁን ያለው የግሽበት ምጣኔ በየትኛውም መስፈርት ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ቢታወቅም፤ ለዚህ የግሽበት ምጣኔ ባለፉት ዓመታት ኢኮኖሚውን የፈተኑት ተደራራቢ ተግዳሮቶች ድምር ውጤት መሆኑን ግን ከግንዛቤ ማስገባት ግድ ይላል። በተለይም የነዳጅ ዘይትን ጨምሮ በዓለም አቀፍ የሸቀጦች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ እንዲሁም በሁቲዎች እንቅስቃሴ ምክንያት የቀይ ባህር የንግድ መተላለፊያ ኮሪዶር ላይ የተፈጠረው ችግር ያስከተለው የማጓጓዣ ወጪ ጭማሪ ለተከሰተው የዋጋ ንረት አሉታዊ ሚና ተጫውተዋል። ከዚህም ባለፈ ኢትዮጵያ በልዩ ሁኔታ በገጠሟት ተግዳሮቶች፡- በአንዳንድ አካባቢዎች የተከሰቱ ግጭቶች፤ ድርቅ እና የምርት እና የአቅርቦት መስተጓጎሎች እንዲሁም መንግስት ከለጋሾች እና አበዳሪዎች ያገኝ የነበረውን የውጭ ምንዛሬ የለማገኘቱ በውጭ ምንዛሬው ላይ የተፈጠረው ጫና እና የተፈጠሩት ውጫዊና ውስጣዊ ተግዳሮቶች ጥብቅ ያልሆነ የፊሲካል/የገንዘብ ፖሊሲ ማሥከተላቸው ለዋጋ ንረቱ የራሳቸውን አስተዋፅኦ እንዳበረከቱ እሙን ነው።

በነዚህ ምክንያቶች በኢትዮጵያ የተከሰተው የዋጋ ንረት ከሌሎች ተመሳሳይ ሃገራት ካጋጠው የግሽበት ምጣኔ በተለየ ከፍተኛ ተግዳሮት ፈጥሯል። ይህ የግሽበት ምጣኔ ስር እንዳይሰድ እና የመጨመር አዝማሚያውን ለመቀልበስ ብሎም የዋጋ ንረቱን በዘላቂነት በቁጥጥር ስር ለማዋል መንግስት አስፈላጊ የሆኑ የፊሲካልና የገንዘብ ፖሊሲዎችን መተግበር፣ የምግብ ምርት እና ምርታማነትን መጨመር፣ በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ያለውን የሰላም ሁኔታ ማሻሻልን ጨምሮ የአቅርቦት፣ የንግድ ሥርዓትና ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ በጥናት የተለዩ የተቀናጁ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል። በተለይም በብሔራዊ ባንክ በኩል ያላሳለሰ ጥረት በማደረግ ላይ ሲሆን፤ ባንኩ ከሌላ ጊዜ በተለየ ሁኔታ የዋጋ ንረትን መቆጣጠርን ዋና ትኩረቱ አድርጎ አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል። ባንኩ እየወሰዳቸው ካሉ እርምጃዎች መካከል፡- ለ2016 በጀት ዓመት የብድር እድገትን በ 14 መቶኛ መገደብ፣ መንግስት ከባንኩ የሚወሰደውን ቀጥተኛ ብድር ከቀደመው ዓመት አንድ ሶስተኛ ላይ መገደብ፣ የንግድ ባንኮች የጥሬ ገንዘብ እጥረት በሚያጋጥማቸው ጊዜ ከብሔራዊ ባንክ የሚበደሩበትን የወለድ ምጣኔ ከ16 መቶኛ ወደ 18 መቶኛ መጨመር ይጠቀሳሉ።

በ2015 በጀት ዓመት የሸቀጥ የወጪ ንግድ አፈጻጸም በ2014 በጀት ዓመት የተመዘገበውን የ4.1 ቢሊዮን ዶላር አመርቂ እመርታ መድገም ሳይቻል የቀረ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው የ3.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ካለፈው አመት አንጻር የ11.8 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል። የዚህ ደካማ የወጪ ንግድ አፈጻጸም በሁሉም ዋና ዋና የወጪ ንግድ ሸቀጦች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፤ በቅደም ተከተል የቡና፣ የወርቅ፣ የአበባ እና የጨርቃጨርቅ የወጪ ንግድ ገቢ የ6.3፣ የ72.4፣ የ11.1 እና የ15.3 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል። አምናም ቅናሽ አሳይቶ የነበረው የወርቅ የወጪ ንግድ ገቢ በ2015 በጀት ዓመት ከፍተኛ ቅናሽ ማሳየቱ በበጀት ዓመቱ ለተመዘገበው ዝቅተኛ የወጪ ንግድ ገቢ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማበርከቱም ባሻገር፤ ዘርፉ ከአጠቃላዩ የሸቀጥ የወጪ ንግድ ገቢ አምና ከነበረው የ13 በመቶ ድርሻ ወደ 4 በመቶ አሽቆልቁሏል። በንፅፅር የቡና ድርሻ ከ35 በመቶ ወደ 37 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። በበጀት ዓመቱ ለተመዘገበው ደካማ የወጪ ንግድ ገቢ አፈጻጸም ዋነኛ ምክንያቶች የአለም አቀፍ የሸቀጦች ዋጋ መዋዠቅ፣ የህገወጥ እና ኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት፣ የኢትዮጵያ ከAGOA መታገድ፣ የጸጥታ ችግር እንዲሁም ሌሎች በንግድ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ማነቆዎች ከፍተኛ ድርሻ አለቸዉ። ከዚህም በተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና የምጣኔው ለላኪዎች ሳቢ አለመሆን የራሱ አሉታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው መገመት አያዳግትም።

በተመሳሳይ ለገቢ ንግዱ የወጣው ወጪ (import bill) ከአምናው አንጻር የ5.2 በመቶ ቅናሽ በማሳየቱ የንግድ ሚዛኑ የተወሰነ ማሻሻል አሳይቷል። ይሁን እንጂ በ2015 በጀት ዓመት የተመዘገበው የ13.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የንግድ ሚዛን ጉድለት በ2013 በጀት ዓመት ከነበረው የ2.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጭማሪ አሳይቷል። የንግድ ሚዛኑ ጉድለት እንደሰፋ መቆየት በውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እና ፍላጎት መካከል ያለውን ክፍተት በማስፋት የብር የውጭ ምንዛሬ ምጣኔ ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ይገኛል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የውጭ ምንዛሬ ክምችትን ለመጨመር ብሎም የውጭ ምንዛሬ ምጣኔውን በትይዩ ገበያው ካለው ምጣኔ ጋር ያለውን ልዩነት በፖሊሲ ለማጥበብ የሚደረገውን ጥረት አዳጋች አድርጎታል።

ለገቢ ዕቃዎች የወጣውን ወጪ በዋና ዋና የገቢ ዕቃዎች ከፋፍለን ስናይ፤ በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው የገቢ ንግድ ወጪ ቅናሽ ሙሉ በሙሉ በፍጆታ ዕቃዎች ወጪ በ 22.4 በመቶ መቀነስ ምክንያት የመጣ መሆኑን እንገነዘባለን። ይህ ቅናሽ መንግስት እጅግ ወሳኝ ባልሆኑ የገቢ ዕቃዎች (non-essential import) ላይ ያስቀመጠው ጊዜያዊ

ክልከላ፣ ከውጭ ምንዛሬ እጥረት (import compression) እንዲሁም የገቢ እቃዎችን በሃገር ውስጥ ምርት ለመተካት (በተለይም በስንዴ እራስን መቻል እንቅስቃሴ) ጋር ተጣምሮ የመጣ መሆኑን መገመት ይቻላል። ከዚህ በተቃራኒ ለካፒታል ዕቃዎች እና ነዳጅ የወጣው ወጪ በቅደም ተከተል የ 25 እና 15 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

በአጠቃላይ የንግድ ሚዛን መዛባትን ለማስተካከል የወጪ ንግዱን መሰረት ማስፋትና በግብርና ሽቀጦች ላይ ያለውን ጥገኝነት መቀነስ አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ፤ ለነዳጅ እና የፍጆታ ዕቃዎች ሀገሪቷ የምታወጣው የውጭ ምንዛሬ የሚቀንስበት መንገድ ላይ መስራት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ነዳጅ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ ማዋልና የፍጆታ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ ምርት በመጨመር መተካት ላይ መስራት፤ ለዚህም ምቹ የፖሊሲ ከባቢ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ማስመር ያስፈልጋል። በዚህ አግባብ የሀገሪቷን የውጭ ምንዛሬ ክምችት መጨመር ካልተቻለ አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ከባድ ያደርገዋል።

በ2015 በጀት ዓመት የተመዘገበው የገንዘብ አቅርቦት የዕድገት ምጣኔ ከ2014 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር 23.95 በመቶ ሲሆን፤ ይህም አምና ከነበረው ዕድገት ጋር ሲነጻጸር የ3.2 መቶኛ ነጥብ መሻሻል አሳይቷል። ሆኖም ይህ የሰፊ ገንዘብ (M2) የዕድገት ምጣኔ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ ከተቀመጠው በአማካኝ በየአመቱ 21 በመቶ የሆነ ዕድገት አንጻር ከፍ ያለ በመሆኑ፤ የዋጋ ንረቱን ከመቆጣጠር ረገድ ተጨማሪ ስራዎችን እንደሚጠይቅ ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል። ካለፈው አመት የተሻለ ቢሆንም፤ የሃገር ውስጥ ብድር በ24.1 በመቶ መስፋፋት ዋናው የገንዘብ አቅርቦት መጨመር ገፊ ምክንያት መሆኑን ማየት ይቻላል። በአገር በቀሉ የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም በታቀደው መሰረት መንግስት ከሀገር ውስጥ የሚበደረውን ብድር በከፍተኛ ሁኔታ መገደብ እና በተላይም ከብሔራዊ ባንክ የሚወስደውን ቀጥተኛ ብድር ቀስ በቀስ ሙሉ ለሙሉ በማቆም የበጀት ጉድለቱን ለዋጋ ንረት በማይዳርጉ የአሸፋፈን (financing) ሥርዓቶች ለመሸፈን ታስቦ አብዛኛውን የመንግስት ግምጃ ቤት ሰነድ በመሸጥ ከሚገኝ ብድር በመጠቀም መሸፈን የተቻለ ቢሆንም፤ ሀገሪቷ በገጠሟት ተደራራቢ ተግዳሮቶች ምክንያት ይሄንን ተግባራዊ ማድረግ አዳጋች ሆኖ ቆይቷል።

ከባንክ ውጭ ያለ ገንዘብ (Currency Outside Banks) በበጀት ዓመቱ ቀነስ ያለ (የ22.4 በመቶ) የዕድገት ምጣኔ ማሳየቱ አበረታች ቢሆንም፤ የዋጋ ንረትን ለመቀነስ ከተቀመጠው ዓላማ አንጻር አሁንም ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን ከግንዛቤ ማስገባት

ያግድ ይላል። በባንክ ተቀማጭ ገንዘብ (bank deposit) በ2015 በጀት ዓመት 1.9 ትሪሊዮን የደረሰ ሲሆን፤ ይህም ከአምናው አንጻር የ24.1 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ለዚህ ዕድገት የባንኮች ተደራሽነት መጨመር እና የቁጠባ ባህል መሻሻል የራሳቸውን አሰዋጽኦ እንደሚኖራቸው ቢታመንም፤ ይህ ሁኔታ በዘላቂነት እንዲቀጥል በነጋቲቭ ዉስጥ ያለውን የእውነተኛ የወለድ ምጣኔ (real interest rate) የዋጋ ንረቱን በመቆጣጠር ማስተካከል ያግድ እንደሚል ማስመር ያስፈልጋል።

የፋይናንስ ዘርፉን ከማሳደግ አኳያ የካፒታል ገበያን ለማቋቋም የተወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በ2013 በወጣ ዓዋጅ የካፒታል ገበያ ምስረታ ከታወጀ በኋላ፤ የኢትዮያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን የካፒታል ገበያውን ለማስጀመር የሚያስፈልጉ የተለያዩ የቁጥጥር ማዕቀፎችን (regulatory framework) በማዘጋጀት ላይ ሲሆን፤ ለካፒታል ገበያው አገልግሎት ሰጪ አካላት ፍቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ተዘጋጅቷል። ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ የሰነዶች ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) ተቋቁሞ የሰነድ ግብይት ለማስጀመር አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል።

3 ያለፉት ዓመታት የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም (2013-2015)

3.1 የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም

3.1.1 የመንግስት ገቢ አፈጻጸም

በለፉት ዓመታት የመንግስት የገቢ አሰባሰብ ከዓመት ወደ ዓመት መጠነኛ መሻሻሎች የተስተዋለበት ነበር፡፡ ከዚህ አኳያ ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም ባሉት ሦስት ዓመታት አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ገቢ በአማካይ የ24.8 በመቶ ዕድገት ሲያስመዘግብ፤ ከታክስ የተገኘው ገቢም በአማካይ በ24.2 በመቶ ለማደግ ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ተመሳሳይ ወቅት ታክስ ያልሆኑ ገቢዎችም በአማካይ 28.5 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ የእነዚህን ገቢዎች የመጨመር አዝማሚያ አበረታች ቢሆንም፤ በወቅቱ ከነበረው የዋጋ ንረት አንጻር (in real terms) አፈጻጸሙ ደካማ እንደነበር መገንዘብ ያስፈልጋል። የውጭ ዕርዳታ አሰባሰብ በቀደሙት ዓመታትም ቢሆን ከአጠቃላይ ዓመታዊ የመንግስት ገቢ ያለው ድርሻ ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር ወጥ የሆነ ዕድገት የሚስተዋልበት አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ በተለይ ከ2010 እስከ 2012 በጀት ዓመት ከፍተኛ ሊባል የሚችል ተከታታይ ዕድገት ማስመዝገቡን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል የነበረውን ጦርነትን ተከትሎ የልማት አጋሮች ለበጀት መሸፈኛ ይዉል የነበረውን ቀጥተኛ የበጀት ድጋፍ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በማቆማቸው ምክንያት በ2013 እና 2014 በጀት ዓመታት የውጭ ቀጥተኛ የበጀት ድጋፍ ዕድገት በቅደም ተከተል የ15.7 እና 22.2 በመቶ አሽቆልቁሎ የነበር ሲሆን፤ በ2015 በጀት ዓመት ከዚህ ምንጭ ምንም አይነት ገቢ አልተገኘም፡፡

ከታክስ የሚሰበሰብ ገቢ ከአጠቃላይ የመንግሰት ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስድ ሲሆን፤ ባለፉት ሦስት የበጀት አመታትም በአማካይ የ82.3 በመቶ ድረሻ ነበረው፡፡ ይህ የአገር ውስጥ ገቢ የሀገራችንን የኢኮኖሚ ዕድገት በዘላቂነት በማስቀጠል የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና የልማት ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ ዋነኛውና አስተማማኝ የሆነው የገቢ ምንጭ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር መንግስት የተለየዩ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ የአገር ውስጥ ገቢ አሰባበሰብን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግን እና ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሽቆልቆል ላይ የሚገኘውን የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ጥመርታ (Tax-GDP ratio) የሚያሽቆለቁልበትን ምጣኔ ለመቀነስ ብሎም ዕድገት ማስመዝገብ እንዲጀምር በርካታ የታክስ ማሻሻያ ስራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሦስት ዓመታት

በታክስ ፖሊሲና በታክስ አስተዳደር ዙሪያ በተተገበሩ ማሻሻያዎች በአጠቃላይ የአገር ውስጥ ገቢ እንዲሁም በታክስ ገቢ አሰባሰብ ላይ አንጻራዊ የሆነ መሻሻል የታየ ቢሆንም፤ አገራችን ባጋጠማት ውጫዊና ውስጣዊ ተግዳሮቶች የተነሳ የገቢ አሰባሰብ አፈጻጸሙ በተቃደዉ ልክ ሊሄድ አልቻላም፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ ከ2013-2015 በጀት ዓመታት ሀገራዊ የመንግስት ገቢ አፈፃፀም

በቢሊዮን ብር

	2013	2014	2015	አማካይ የገቢ ድርሻ	አማካይ ዓመታዊ ዕድገት
ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢና ዕርዳታ	449.7	525.8	717.2	100	22.4
ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ	415.4	499.1	685.1	94.3	24.9
የታክስ ገቢ	361.7	436.8	595.2	87.2	24.4
ቀጥታ ታክስ	170.8	206.8	265.4	46.4	26.2
ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች	190.9	231.5	329.8	53.7	23.4
የአገር ውስጥ ቅጥታ ያልሆኑ ታክሶች	84.3	100.2	161.2	45.4	28.9
የገቢ ዕቃዎች ታክሶች	106.6	131.3	168.6	54.6	19.3
ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች	53.7	62.3	89.9	12.8	28.6
የውጭ ዕርዳታ	34.3	26.7	32.1	5.7	-5.9
	ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ (በመቶኛ)				
ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢና ዕርዳታ	10.4	8.5	8.2	9.0	
ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ	9.6	8.1	7.9	8.5	
የታክስ ገቢ	8.3	7.1	6.8	7.4	
ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች	1.2	1.0	1.0	1.1	
የውጭ ዕርዳታ	0.8	0.4	0.4	0.5	

በአጠቃላይ በተለያዩ ተግዳሮቶች መሀል እንኳን ላለፉት ሦስት ዓመታት አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ገቢ በተለይም የታክስ ገቢ ላይ ተከታታይነት ያለው ዕድገት የተመዘገበ ቢሆንም፤ ኢኮኖሚው ካለው እምቅ አቅም አንጻር ተስተካካይ የሆነ የታክስ ገቢ በማመንጨት የታክስ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በሚጠበቀው ልክ ማሰደግ አልታቻለም፡፡ ለአብነትም በ2007 በጀት ዓመት ደርሶበት ከነበረው የ12.7 መቶኛ ጥምርታ፤ በ2015 በጀት ዓመት ወደ 6.8 መቶኛ ወርዷል፡፡

ለዚህም ተጨማሪ የታክስ ፖሊሲና የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎችን በማተግበር የታክስ መሰረትን ማስፋት ተገቢ ይሆናል፡፡ ከነዚህ ዉስጥ ታክስ መረቡ ያልገቡትን

ማስገበት፣ የታክስ ስወራን መቀነስ፤ የሚሰጡ የታክስ ማበረታቻዎች የሚያስከትሉትን ብክነት መቀነስ፣ የታክስ መክፈል ግንዛቤ እና ባህልን ማሳደግ፣ የግብር ክፍያ ሥርዓቱን ማዘመን ላይ አጠናክሮ መስራት ያስፈልጋል።

3.1.2 የመንግስት ወጪ አፈጻጸም

ጠቅላላ የመንግስት ወጪ ባለፉት ሦስት ዓመታት በአማካይ የ24.7 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን፤ በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ የ20.2 በመቶ ብቻ ዕድገት አሳይቷል። ይሄንን የጠቅላላ የመንግስት ወጪ እድገት ባለፉት አመታት ሲያስመዘግብ ከነበረው እድገትም ሆነ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት እድገት ወይንም በወቅቱ ካለው የዋጋ ንረት አንጻር በማየት መንግስት ጥብቅ የፊስካል ፖሊሲ መከተል ላይ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በአጠቃላይ የመንግስት የወጪ ፖሊሲ አብዛኛውን የመንግስት ገቢ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት በተለይም በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ ማዋልን ማዕካል በማድረግ የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦትን በማሳደግ እና ፈጣንና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማስፈን የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ከፍ ማድረግን እንደዋነኛ ግብ የያዘ መሆኑ ይታወቃል።

ከዚህ አንጻር ቀድም ባሉት ዓመታት ከአጠቃላይ ዓመታዊ የመንግስት በጀት ላቅ ያለ ድርሻ ለካፒታል ወጪ እንዲውል ሲደረግ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ከ2009 በጀት ዓመት ወዲህ የመደበኛ ወጪ ከጠቅላላ ዓመታዊ የመንግስት ወጪ ያለው ድርሻ ከካፒታል ወጪ እየጨመረ መጥቷል። በመሆኑም ባለፉት ሦስት ዓመታት (2013-2015) የመደበኛ ወጪ በአማካይ ከጠቅላላ የመንግስት ዓመታዊ ወጪ ከነበረው ድርሻም ሆነ በአማካይ ካሳየው ዓመታዊ ዕድገት አንጻር፤ ከካፒታል ወጪ እየላቀ መምጣቱን ማየት ይቻላል። ባለፉት ሶስት ዓመታት የመደበኛ እና ካፒታል ወጪዎች በቅደም ተከተል የ28.5 እና የ20.0 በመቶ አማካይ ዕድገት ሲያስመዘግቡ፤ በዚህ እረገድ በ2015 በጀት ዓመት መሻሻል የታየ ሲሆን፤ የካፒታል ወጪዎች ዕድገት (33.1 በመቶ) ከመደበኛ ወጪዎች ዕድገት (13.5 በመቶ) የ19.6 መቶኛ ነጥብ ብልጫ አሳይቷል። ከአጠቃላይ የመንግስት ወጪ ካላቸው ድርሻ አንጻር ደግሞ፤ ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማካሄጃ የወጣው ወጪ በ2014 በጀት ዓመት ከነበረበት የ34 በመቶ ድርሻ በ2015 በጀት ዓመት ወደ 37.9 በመቶ ሊጨምር ችሏል።

ሀገራችን የተለያዩ ክፍሎች ለተከሰቱ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም በዚሁ ምክንያት ለተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን የሰብዓዊ ድጋፍ

ለማድረግ የሚያስፈልገው የወጪ ፍላጎት በመጨመሩ እና በመጠባበቂያ በጀት ብቻ ሊሸፈን የሚቻል ባለመሆኑ በተወሰነ ደረጃ የወጪ ማሸጋሸግ /expenditure reprioritization/ ማድረግ በማስፈለጉ በመንግስት የወጪ ፖሊሲ አቅጣጫ አፈጻጸም ላይ ጫና ፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም ባለፉት ሦስት ዓመታት የአገር ውስጥና የውጭ ዕዳ ክፍያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨረ መምጣት ለመደበኛ ወጪው ድርሻ መጨመር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

በነዚህ ምክንያቶች ሳቢያ መንግስት ለድህነት ተኮር ዘርፎች በሚመደበው በጀት ላይም ጫና የተፈጠረ ሲሆን፤ ባለፉት ሶስት አመታት ለዘርፉ የወጣው ወጪ ከአጠቃላዩ የመንግስት ወጪ ያለው ድርሻ ከአመት ወደ አመት ቅናሽ በማሳየት በ2015 በጀት አመት 48.3 በመቶ ደርሷል። ይሁን እንጂ ባለፉት ሶስት ዓመታት ለድህነት ተኮር ዘርፎች የወጣው ወጪ ከአጠቃላይ የመንግሰት ወጪ በአማካይ 51.6 በመቶ ድርሻ የነበረው ከመሆኑም ባሻገር፤ በ2015 በጀት ዓመት የ17.8 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ይህም አገራችን ባለፉት ሶስት ዓመታት ከነበረችበት ነበራዊ ሁኔታ አንጻር እንኳን ለድህነት ተኮር ዘርፎች ከፍተኛ ድርሻ መሰጠቱ እና ዓመታዊ ዕድገት ማስመዝገቡ፤ መንግሥት ለዘርፉ የሚሰጠውን ትኩረት እና ድህነትን በስፋት ለመቀነስ ያለውን የጸና አቋም በግለጽ የሚያረጋግጥ ነው (ሠንጠረዥ 2)፡፡

ሠንጠረዥ 2፣ ከ2013-2015 ሀገራዊ የመንግስት ወጪ አፈጻጸም

በቢሊዮን ብር

የወጪ ዓይነት	2013	2014	2015	አማካይ እድገት
ጠቅላላ ወጪ	599	785.3	943.9	776.1
መደበኛ ወጪ	363.6	518.1	588.1	489.9
ካፒታል ወጪ	235.4	267.2	355.8	286.1
የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ	342.5	387.5	456.6	395.5
ትምህርት	141.2	169.4	196	168.9
ጤና	63	68.4	72.7	68.0
ግብርና	50.3	48.5	53.9	50.9
ውሃ	24.8	38.3	53.3	38.8
መንገድ	63.2	62.9	80.7	68.9
	አመታዊ እድገት በመቶኛ			
ጠቅላላ ወጪ	22.7	31.1	20.2	24.7
መደበኛ ወጪ	29.5	42.5	13.5	28.5
ካፒታል ወጪ	13.4	13.5	33.2	20.0
የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ	**16.0**	**13.1**	**17.8**	**15.7**
ትምህርት	14.7	20.0	15.7	16.8
ጤና	23.5	8.6	6.3	12.8
ግብርና	24.8	-3.6	11.1	10.8
ውሃ	-7.1	54.4	39.2	28.8
መንገድ	17.0	-0.5	28.3	14.9
	ድርሻ በመቶኛ			አማካይ ድርሻ
መደበኛ ወጪ	60.7	66.0	62.3	63.0
ካፒታል ወጪ	39.3	34.0	37.7	37.0
የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ	57.2	49.3	48.4	51.6

3.1.3 የበጀት ጉድለት እና የመንግስት ዕዳ ሁኔታ

መንግስት የወጪ ፍላጎቱን በሀገር ውስጥ በሚሰበሰብ ገቢ ለመሸፈን በሚያደርገው ጥረት የበጀት ጉድለት እንደሚፈጠር ይታወቃል፣ ዋናውና መሰረታዊ ነገር የጉድለቱን መጠንና ጉደለቱ የሚሸፈንበትን መንገድ የማክሮ ኢኮኖሚውን መረጋጋት ባስጠበቀ መልኩ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የመጀመሪያው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ካካተታቸው የፊሲካል ሪፎርሞች መካከል አንዱ የመንግስትን የፊሲካል ጉድለት ከጠቅላለ አገራዊ ዓመታዊ ምርት ያለዉ ከ 3 በመቶ እንዳይበለጥ ማድረግ እና አሸፋፈኑን የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን በሚያሰፍን መልኩ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን፣

የሁለተኛው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትኩረትም ይኼንኑን በማጠናከር ኢኮኖሚው በፍጥነት እንዲያገግም ማስቻል እንዲሁም ለአዳዲስ የዕድገት ዕድሎች በር በመክፈት አስር ዓመቱ ብሔራዊ የልማት ዕቅድ እንዲሳካ ማገዝ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በአገራችን ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ከወረርሽኙ፣ ከተፈጥሮ አደጋ እና ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ በተፈጠረው የፊሲካል ጫና ምክንያት የበጀት ጉድለቱ እየሰፋ ሄዶ በተለይም በ2014 በጀት ዓመት 4.2 በመቶ ደርሶ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ በተለይም የበጀት ጉደለቱን ለመሸፈን ከብሔራዊ ባንክ በቀጥታ የተወሰደው ብድር ከፍተኛ ዕድገት አሳይቶ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል የነበረው ጦርነትና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ፈጥረውት የነበረው የፊሲካል ጫና በአንጻራዊነት በመቀነሱ እንዲሁም መንግስት በወሰደው ጠንካራ የፊሲካል ፖሊሲ እርምጃ በ2015 በጀት ዓመት የበጀት ጉደለቱን ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት ወደ 2.6 በመቶ ማውረድ የተቻለ ተችሏል፡፡

ይህንንም ተከትሎ የበጀት ጉደለቱን ለመሸፈን ከብሔራዊ ባንክ በቀጥታ የተወሰደው ብድር በ2014 በጀት ዓመት ከነበረበት በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በያዝነው የ2016 በጀት ዓመትም የበጀት ጉደለቱ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት እንዳይበልጥ ከፍተኛ የፊሲካልና ሞኒተሪ ፖሊሲ ክትትልና ቁጥጥር እርምጃዎች በመውሰድና በመንግስት በኩል ለበጀት ጉድለት መሸፈኛ ከብሔራዊ ባንክ በቀጥታ የሚወሰድ የቀጥታ ብድር መጠን በሁለት ሶስተኛ ለመቀነስ የተያዘውን አቅጣጫ ተግባራዊነት ለማረጋገጥ እና በቀጣዮቹ ዓመታት የሚኖረውን የብድር ክፍያ ወጪ ፍላጎት ጫና በማጥበብ የሀገሪቱ የመንግስት ዕዳ የስጋት ደረጃ ወደ መካካለኛ እንዲቀንስ ማድረግ እንዲሁም የዋጋ ንረት ምጣኔን ለመቆጣጠር በትጋት ሊሰራባቸው እንዳሚገበ ተሰምሮበት እያተተገበረ ይገኛል፡፡

የመንግስት የውጪ ዕዳ ክምችትን /external debt stock/ ከመቀነስ አንጻር የኤክስፖርት አፈጻጸማችን ተሻሽሎ የሀገሪቱ የመንግስት የውጪ ብድር ዕዳ የስጋት ደረጃ ከከፍተኛነት ወደ መካከለኛ ደረጃ እስከሚሻሻል ድረስ አዳዲስ የንግድ የውጭ ብድሮች (external commercial loan) እንዳይወሰዱ የሚከለክለውን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነው። ከዚህ ባለፈ የዋና ብድርና የወለድ ክፈያዎችን በወቅቱ በመፈጸም እንዲሁም ከውጪ አበዳሪዎች ጋር የዕዳ ሽግሽግ ድርድሮችን በማድረግ አጠቃላይ የዕዳ ክምችት ከሃገራዊ ምርት ያለዉን ድርሻ እንዲቀንስ ማድረግ የሚያስችሉ ጥረቶች እየተደረጉ

ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከትግራዩ ጦርነት ጋር በተያያዘ የዓለም ዓቀፍ ማህበረሰብ በሀገሪቱ ላይ አድረሶት በነበረው ጫና ምክንያት የውጭ ዕዳ ሽግሽግም እንደተጠበቀው ባለመሄዱ የውጭ ዕዳ ክፍያ ጫናም ከፍተኛ ስጋት ሆኗል፡፡ የሀገር ውስጥ ዕዳም ቢሆን እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ለመንግስት ዕዳ እንደ ስጋት ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ሆኖም ባለፉት ቅርብ ዓመታት አገሪቱ ለገጠሟት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምላሽ ከመስጠት ጋር በተያያዘ የመንግስት ወጪ ከፍተኛ ጭማሪ በማሳየቱና የመንግስትም ገቢ በተቃደዉ ልክ ከላመሰብሰቡ ጋር ተያይዞ መንግስት በዕቅድ የያዛቸው የልማት ፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ ተጽዕኖ ከማሰደሩም በላይ የመንግስት የሀገር ውስጥ ዕዳ ክምችትና የብድር ክፍያ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ጭማሪ እንዲያሳይ አድርጓል፡፡ መንግስትም ይሄንን ጉዳይ እንደ አንድ የፊሲካልና የኢኮኖሚ ስጋት በመውሰድ ስጋቱ ወደ ኢኮኖሚ አደጋነት እንዳይሸጋገር ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን የፊሲካል እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ በአጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚው አፈጻጸም ግምገማ እንደሚያሳየው አገራችን ገጥሚት በነበሩት ውጫዊና ውስጣዊ ተግዳሮቶች የሃገሪቱ የልማት ዕቅዶችና ማሻሻያዎች በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ የነበረውን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ችግር (የዋጋ ንረት፣ የብድር ስጋት እና የዉጭ ምንዛሪ ሁኔታዎችን) ቶሎ ለማቅረፍ አዳጋች አድርጓታል፡፡ ስለሆነም ይህ የመካከለኛ ዘመን የፊሲካል ፖሊሲ ማዕቀፍ ዝግጅት ይሼንን እውነታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሲሆን፤ ትኩረቱም ይሼንን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባትን በቶሎ ለማስተካከል የሚያስችሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎች መተግበር ላይ ሆኗል፡፡

3.1.4 የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር

የመንግስትን የፊሲካል ፖሊሲ በውጤታማነት ተግባራዊ ለማድረግ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ችግር ፈች የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ይታመንበታል፡፡ በዚህ ረገድ ውጤታማ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን በሥራ ላይ ማዋል የህዝብን ሀብት በአግባቡና ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው ሥርዓት መምራት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ እነዚህን ተግባራት የሪፎርም ፕሮግራም በመቅረጽ ወጥነት ባለው መንገድ ሥራ ላይ ለማዋል ተሞክሯል፡፡ ይህ የሪፎርም

ፕሮግራም በበጀት፣ በክፍያ፣ በሂሳብ፣ በውስጥና በውጭ አዲት እንዲሁም በፋይናንስ መረጃ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ዘመናዊና ቀልጣፋ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ አገር አቀፍ አሰራሮችን ለመዘርጋት አስችሏል፡፡ ከነዚህም የተከናወኑ ተግባራት መካካል:-

- ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ የመንግስት ፋይናንስ የሪፎርም ስራዎች ያመጡትን ውጤቶችና ክፍተቶችን የሚለይ ጥናት የተከናወነ ሲሆን ከዚህ ጥናት ላይ በመመስረት አዲስ የመንግስት ፋይናንስ ሪፎርም ስትራቴጂ እንዲቀረፅ ተደረጎ ወደስራ ተገብቷል። በተመሳሳይ የአደጋ ስጋት ፋይናንስ ስትራቴጂ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ተዘጋጅቶ ለውሳኔ ለመንግስት ቀርቧል
- የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የህግ ማዕቀፍ በማሻሻል ሥርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ለረጅም አመታት ሲያገለግሉ የነበሩ የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያዎችን የማሻሻል ስራ ተጀምሮ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል
- የፕሮግራም በጀት አሠራር ሥርዓትን ወደ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ለማውረድ የሚያስችል ፕሮቶታይፕ የአሰራር ማንዋልና ሞጁል ተዘጋጅቶ ለአፈፃፀም ለክልሎች ተልኳል
- የመንግስት ግዥ ስርዓትን በማዘመን ቀልጣፋ፣ ግልፅና ውጤታማ ግዥዎችን ለመፈፀም የሚያስችለው የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት (Electronic Government Procurement) በሁሉም የፌደራል መ/ቤቶች ተደራሽ ሆኗል፡፡. በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ 9 ወራት የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ (e-GP) ሲስተምን በመጠቀም 13,985 ጨረታዎችን በግንዘብ ከብር 113 ቢሊዮን በላይ የሚያወጡ ግዥዎች በ e-GP እየተፈፀሙ ይገኛል፡፡
- የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች ክፍያዎች ቀጥታ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት እንዲፈፅሙ በማድረግ ባለፉት 9 ወራት 349,027 ትራንዛክሽን የተካሄደ ሲሆን ከብር 153 ቢሊዮን በላይ ወጪዎችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ክፍያ ለመፈፀም ተችሏል፡፡
- በመንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደሩን በይበልጥ ለማሻሻል የሚረዳው የትሬዠሪ ነጠላ አካዉንት/TSA/ ስርዓት ለማስጀመር የቅድመ ዝግጅት ስራዎች የተጀመረ ሲሆን በሌላ በኩል አለም አቀፍ ፐብሊክ ዘርፍ የሂሳብ አያያዝ እና አቀራረብ ደረጃዎች /IPSAS/ ለመተግበር በመንግስት ከፍተኛ አመራር ደረጃ የሚመራ

የስትሪንግ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴው ስብሰባ በማድረግ በቀጣይ የሚሰሩ ስራዎችን አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

- በበጀት ዓመቱ የተቀናጀ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ስርዓት (IFMIS) ዝርጋታ የማከናወን ስራ የቀጠለ ሲሆን በ15 ተጨማሪ መ/ቤቶች ዝርጋታ ተካሂዷል፡፡ አጠቃላይ ሽፋኑም 117 የፌደራል መንግስት ተቋማት እና 110 ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ተደራሽ የሆነ ሲሆን በቀጣይ በ43 የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች (IFMIS) እና የፀጥታ ተቋማት ለመዘርጋት የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አማካሪ ቅጥር ተፈፅሟል፡፡ በተጨማሪም ኢፍሚስ በተዘረጋላቸው ባለበጀት መ/ቤቶች ለሚገኙ ሴት 627 እና ወንድ 442 በድምሩ 1069 ባለሙያዎች መሠረታዊ የኢፍሚስ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የኢትዮጵያ ሂሣብ ባለሙያዎች ማሠልጠኛና ብቃት ማረጋገጫ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ በማዘጋጀት ለውሳኔ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቦ ውሳኔ እየተጠበቀ ይገኛል
- ዜጎች ስለሀገራዊ በጀት ዝግጅት ሂደትና መረጃ አውቀውና ተረድተው በበጀት ትግበራ ሂደት ላይ በባለቤትነት እንዲሳተፉና እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ በህግ አውጭው አካል ለ2016 በጀት ዓመት የፀደቀውን በጀት ለሁሉም ዜጎች በቀላልና ሊገባ በሚችል መልኩ አዘጋጅቶ ለማሠራጨት በታቀደው መሠረት የዜጎች የበጀት መረጃ ሠነድ (Citizens Budget) ተዘጋጅቶ መረጃው ተሰራጭቷል፡፡ በተጨማሪም በፌዴራል እና ክልል ደረጃ የፋይናንስ ግልፅነትና ተጠያቂነት ሪፎርም ስራዎች ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡
- የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ለማሻሻል የተለያዩ የማቴርያል እና ቴክኒክ ድጋፎች ተደርጓል፡፡

4. የ2016 በጀት አፈጻጸም ዕይታ

4.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ አፈጻጸም የኢኮኖሚ ዕድገት

በመግባደድ ላይ ባለው 2016 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው የ7.9 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ግብ መያዙ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በዓለም ዓቀፍ ሁኔታ በተከሰተው ከፍተኛ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ምክንያት፣ እንዲሁም በሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ምክንያት የአለም የንግድ ሰንሰለት መዛባት እና የመሳሰሉት ምክንያቶች እንዲሁም ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው መጠነ ሰፊ ጦርነት ያስከተለው የኢኮኖሚ እና የፊሲካል ጫና አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ቀደም ሲል ከተገመተው በታች እንዳይሆን ከፍተኛ ርብርብ በመደረግ ላይ ነው። በመሆኑም መንግስት እና ባለድርሻ አካላት እያደረጉት ባለው ርብርብ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ የማይበገር በመሆን የ7.9 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በ2017 በጀት ዓመት 8.4 በመቶ ዕድገት እንደሚመዘገብ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

የሸቀጦች የወጪ ንግድ:- በመግባደድ ላይ በሚገኘው 2016 በጀት ዓመት የሸቀጦች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም አንጻር ሲታይ ቅናሽ አሳይቷል። በዚህም መሰረት በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ከሸቀጦች የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) 2,167.2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህም በ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተገኘው 2,376.1 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ጋር ሲነፃጸር በ208.9 ሚሊዮን ዶላር (በ8.8 በመቶ) ያህል ቅናሽ ማሳየቱን መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም በመጠን ሲታይ እንደዚሁ ከባለፈው ዓመት አንጻር መጠነኛ ቅናሽ ማሳየቱን መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ በመሆኑም በቀሪዎቹ ወራት ወጪ ንግዱን ላማሻሻል መሰራት ያለበትን ሁሉ በማድረግ አፈጻጸሙን ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡

የዋጋ ንረት፦ በመጋቢት ወር 2016 ዓ.ም የተመዘገበው የ12 ወራት አማካይ (12 Months Moving Average) አገራዊ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ዕድገት 28.9 በመቶ መሆኑን የዋጋ ናሙና ዳሰሳ ጥናት አመላክተዋል፡፡ የዚህ ዕድገት ምንጭ ምግብና ምግብ ነክ ባልሆኑ ሸቀጦች ዋጋ ሲሆን፣ የምግብ ነክ የ12 ወራት አማካይ አገራዊ አጠቃላይ የዋጋ ዕድገት 29.3 በመቶ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወር ከተመዘገበው ጋር ሲነፃፀር መጠነኛ (የ5.2 መቶኛ ነጥብ) መሻሻል ሊያሳይ ችሏል፡፡፣ የምግብ ነክ ያልሆኑ ዕቃዎች የዋጋ ግሽበት 28.4 በመቶ ሆኗል፡፡

የዋጋ ግሽበቱን ለመቆጣጠር መንግስት በገንዘብና በፊሲካል ፖሊሲ የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ መቆየቱ ይታወቃል። ከነዚህም መካከል መንግስት ከብሔራዊ ባንክ የሚወሰደውን የቀጥታ ብድር ባለፈው አመት ከወሰደው አንድ ሶስተኛ እንዳይበልጥ ማድረግ፣ ንግድ ባንኮች የብድር ምጣኔያቸው በቀዳሚው አመት ካበደሩት ከ14 በመቶኛ እንዳይበልጥ ማድረግ እና ጥብቅ የሆነ የፊሲካል ፖሊሲ መከተል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎችን በማስገባት እና ለህዝቡ እንዲደርስ በማድረግ የዋጋ ግሽበቱ እንዳይባበስ አድርጓል። ሆኖም የዋጋ ግሽበቱ ከመረጋገት ባለፈ ወደ ነጠላ አሃዝ ማውረድ ያልተቻለው ከውጪ በገባ የግሽበት ዓይነት (Imported Inflation) ሲሆን ይህውም እንደ ኢትየጵያ አብዛኛው የፍጆታ እቃቸውን ከውጪ ሀገራት በሚያስገቡ ሀገራት ላይ ሲደርስ የሚታይ ጫና ነው። ለዚህም የነዳጅ ዋጋ መጨመር፣ የአለም የንግድ ሰንሰለት ሚዛን መዛባት፣ የሩስያና ዩክሬን ጦርነት ዋነኞቹ ናቸው።

4.2 የ2016 በጀት የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም

በ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ከሐምሌ ወር ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ ብር 707.3[1] ቢሊዮን ወጪ ያጸደቀ ሲሆን፤ ይህም ወጪ ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች እንዲሁም ከውጭ ዕርዳታን ጨምሮ በሚገኝ ብር 485.8 ቢሊዮን ገቢ ለመሸፈን የታቀደ ነው። ከዚህ አንጻር የበጀት ጉድለቱ ብር 221.4 ቢሊዮን ሆኖ፤ ጉድለቱ በብር (11.4) ቢሊዮን የተጣራ የውጭ ብድር እና በብር 238.7 ቢሊዮን የተጣራ የአገር ውስጥ ብድር እንደሚሸፈን ታሳቢ ተደርጓል።

በዚሁ በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት የፌዴራል መንግሥት የተጣራ የታክስ ገቢ ብር 313.9 ቢሊዮን ብር ሲሆን፣ ተሰብስቦ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ ይደረጋል ተብሎ ከተቃደዉ ዓመታዊ የታክስ ገቢ ዕቅድ ብር 440.8 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር የ71.2 በመቶ መሆኑን ማየት ተችሏል። ይህም በ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ከተሰበሰበው የታክስ ገቢ አንጻር የ12 በመቶኛ ዕድገት አሳይቷል።

ከወጪ አኳያ በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት የፌዴራል መንግሥት መደበኛ፣ ካፒታልና ለክልሎች ጠቅላላ የበጀት ድጋፍን ጨምሮ በድምሩ ብር 494.8 ቢሊዮን ወጪ ተደርጓል። ይህም በበጀት ዓመቱ ከተያዘው ዓመታዊ የወጪ ዕቅድ ብር 707.3

[1] *ይህ ብር 707.3 ቢሊዮን የፌዴራል መንግሥት በጀት የዋና ዕዳ ክፍያን፣ የፕሮጀክት ዕርዳታን፣ የክልሎች የፕሮጀክት ዕርዳታ እና ብድር ወጪ አይጨምርም።*

ቢሊዮን አንጻር አፈጻጸሙ 70 በመቶ ደርሷል፡፡ በሌላ በኩል በ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረው የወጪ አፈጻጸም ጋር ሲነፃፀር የ8 በመቶ (የብር 36.6 ቢሊዮን) ብልጫ አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ በተያዘው በጀት ዓመት የገቢውም ሆነ የወጪ ፍሰት በጥሩ የፊሲካል ዲሲፕሊን እየተመራ ያለ ሲሆን፤ በተቀሩትም የበጀት ዓመቱ ወራቶች ፍሰቱን ሊያዛባ የሚችል የተለየ የወጪ ፍላጎት የማይኖር ከሆነ የተሻለ የፊሲካል አፈጻጸም እንደሚኖር ይታመናል፡፡

በሌላ በኩል ከጥቂት ወራት ወዲህ በተለየዩ አካባቢዎች በተፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት የፌደራል መንግስት በተዘዋዋሪ መንገድ የሚሰበስበውን የታክስ የገቢ አሰባሰብ ላይ የራሱ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ የበጀት ዓመቱ ሰባት ወራት ከልማት አጋሮች ይገኛል ተብሎ የታቀደው የቀጥታ በጀት ድጋፍ በሚፈለገው ደረጃ እንዳልተገኘ መረጃዎች ያመላክቱ ሲሆን፤ በቀጣዮቹ ወራት ከልማት አጋሮቻቸን ጋር ድርድሮችን በማድረግ ዕቅዱ ይሳካ ዘንድ ትኩረት ተሰጥቶበት እየተሠራ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የቀጣዮቹ ዓመታት የመንግስት በጀት ዝግጅት ዋና የትኩረት አቅጣጫ ይህንን እየታየ ያለውን የፊሲካል ሚዛን መዛባት ስጋት ለማስተካከል ተገቢውን ትኩረት ሊሰጥ የሚገባ ሲሆን፤ አፈጻጸሙንም በቅርበት መከታተልን ይጠበቃል፡፡

5. የ2016 በጀት ዓመት ገቢ፣ ወጪና የወጪ አሸፋፈን

ከዚህ በላይ በቀረቡት የሰነዱ ክፍሎች ከአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም አንጻር የተገኙ ከዚህ በላይ በቀረቡት የሰነዱ ክፍሎች ከአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም አንጻር የተገኙ ዋና ዋና ስኬቶችን፣ እንዲሁም የ2015 በጀት ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚና የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም ዕይታ በሚመለከት በዝርዝር ተዳሰዋል። በመሆኑም እነዚህ ጉዳዮች ከግምት ባስገባ መልኩ የ2016 በጀት ዓመት ዓመታዊ በጀቱ የተዘጋጀ ሲሆን በዋናነትም ባለፉት ዓመታት በተፈጠሩ ውጣ ውረዶች ምክንያት የተዛባውን ማክሮ ኢኮኖሚ የማስተካከል ዓላማን ሰንቆ ነው። በመሆኑም እነዚህ ጉዳዮች ከግምት ባስገባ መልኩ የ2016 በጀት ዓመት ዓመታዊ በጀቱ የተዘጋጀ ሲሆን በዋናነትም ባለፉት ዓመታት በተፈጠሩ ውጣ ውረዶች ምክንያት የተዛባውን ማክሮ ኢኮኖሚ የማስተካከል ዓላማን ሰንቆ ነው። ተፈጥሮ የነበረውን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ለማስተካከል መንግስት ዘርፈ ብዙ እርመጃ እየወሰደ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ የኢኮኖሚ መሻሻያ በመንደፍ ተፈጻሚ ሲሆን ቆይቷል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ባጋጠሙ ዓለም አቀፍ ተግዳሮቶች ምክንያት ቀላል የማይባሉ ሀገሮች ኢኮኖሚያቸው የኋልዮሽ ጉዞ በሚያደርግበት ሁኔታ የሀገራችን ኢኮኖሚ ሳይበገር ወደፊት እንዲሄድ አስችሎታል። በተያዘው በጀት ዓመትም የዚሁን ማሻሻያ ቀጣይ ክፍል በማዘጋጀት ከሚቀጥለው በጀት ዓመት ጀምሮ መተግበር እንደሚጀምር ይጠበቃል። በመሆኑም ልንከተላቸው የሚገቡ የፖሊሲ አቅጣጫዎችም ሆኑ የመንግስት በጀት ዝግጅት ከዚህ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ተገቢ ነው። የፊሲካል ፖሊሲው አቅጣጫ ከላይ የተካተቱትን ማሻሻያዎች ተግባራዊ ከማድረግ ባለፈ የመንግስት በጀት አሁንም ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለመንገድ መሠረተ ልማት፣ ለግብርናና መስኖ፣ ለንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እና በቀጣይ አዲስ ትኩረት ለሚሰጣቸው ዘርፎች ቅድሚያ የሚሰጥ ይሆናል። ሆኖም በነዚህ ዘርፎች ውስጥ የየትኞቹ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሄድ እንደሚገባው መንግስት የፖሊሲ አቅጣጫ ማስቀመጥ የሚገባው ሲሆን፣ ይህም በዝርዝር የበጀት ዝግጅት ወቅት ለማየት ተሞክሯል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ባለፉት ዓመታት መንግሥት በተለይ ለማህበራዊ ዘርፍ በተለይም ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና የልዩ ልዩ ሙያ ማሰልጠኛዎች የሚመረቁ ዜጎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ማደጉ አንድ ጉዳይ ሆኖ፣ ይህንን የሰለጠነውን የሰው ሀይል ሀገሪቱ ባግባቡ እየተጠቀመችበት ነው ወይ የሚለው ጉዳይ በአንክሮ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። በመንግሥት ገቢ አሰባሰብ ረገድም

የታክስ ገቢን ለማሻሻል ዜጎችን በማሳተፍ እና የታክስ ሰብሳቢ ተቋማትን አቅም በማጠናከር፣ ዘመናዊ አስተዳደር በመዘርጋትና የታክስ ትራንስፎርሜሽንን በማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሰራ እምነት ተጥሏል፡፡ በአንጻሩም የፊሲካል ሥርዓቱን ለማጠናከር የመንግስት ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነትን የሚያሻሽሉ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ ሥርዓቶችን በመዘርጋትና በውጤታማነት ሥራ ላይ በማዋል የሀብት ብክነትን ለማስወገድና በጀትን በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችሉ ተግባራት የማከናወኑ ተግባር በተጠናከረ ሁኔታ ቀጣይ ይሆናል፡፡ ይህም የመንግስትን ውስን ሀብት በአግባቡና በውጤታማነት በመጠቀም የማህበራዊና ኢኮሚያዊ አገልግሎቶችን፣ አቅም በፈቀደ መጠን ለህብረተሰቡ ለማድረስ የሚያስችል ይሆናል፡፡ እንደ ባለፉት ዓመታት የ2016 በጀት ዝግጅት እነዚህን ማሻሻያዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንዲሁም በቀጣዮቹ ዓመታት ዕውን ይሆናሉ የተባሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕይታዎችን ታሳቢ በማድረግ ለማዘጋጀት ተሞክሯል፡፡

5.1 ኢኮኖሚያዊና ፊሲካል ታሳቢዎች

5.1.1 ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች

በሀገራችን የሰሜኑ ክፍል የነበረውን ጦርነት ለማስቆም መንግስት የፈጸመውን ቁርጠኛ የሰላም ስምምነት ከሁሉም በላይ በቀጣዮቹ ዓመታት በሀገራችን ሰላም እንደሚሰፍንና ዘመኑም ኢኮኖሚውን መልሶ በመገንባት ላይ ትኩረት በመስጠት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው ከተግዳሮቶች የተላቀቀና ለቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት ምቹ ሁኔታዎች እንደሚፈጠር ታሳቢ በማድረግ፣ ለ2016 በጀት ዓመት ዝግጅት የሚከተሉት ዋና ዋናና ተያያዥ የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች ተደርገዋል፡፡

በዘንድሮ በጀት ዓመት ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሀገራችን ህግ ማስከበርንና የህልውና ዘመቻን ተከትሎ በተከሰተው ሁኔታ ኢኮኖሚው በመዳከሙ፣ የመንግስት ገቢ በመቀነሱ፣ ከልማት አጋሮች የሚገኙት የበጀትና ልማት ድጋፍ በመቋረጡ እንዲሁም ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ በበርካታ አካባቢዎች በርካታ ህዝብ በመፈናቀሉ እንዲሁም የተለያዩ የኢኮኖሚ ተቋማት በመውደማቸው ወይም ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውጭ በመሆናቸው፣ ከፍተኛ ሀብት ለጦርነቱ በመዋሉ የመንግስት የፊሲካል አቅም የተዳከመ ከመሆኑም በላይ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚፈጥር ግልጽ ነው፡፡ እንዲሁም በተወሰኑ የሀገራችን የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የተከሰተው መጠነ ሰፊ የሆነ ድርቅ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ሲሆን፣ ይህም በኢኮኖሚ ዕድገቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ

ያሳድራል፡፡ ምንም እንኳን የግብርና እምቅ ሀብት ባላቸው አካባቢዎች እነዚህ ጉዳቶች በኢኮኖሚው ላይ የሚኖራቸውን ተጽእኖ ለማካካስ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ቢሆንም ጉዳቱን ሙሉ ለሙሉ ማካካስ የሚቻል ባለመሆኑ በያዝነው የ2016 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው ቀደም ብሎ ያድጋል ተብሎ ከተያዘው የ9.6 በመቶ ዕድገት ዝቅ ያለ ምጣኔ ሀብት 7.9 በመቶ ዕድገት እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል፡፡

- የዋጋ ንረት ለማዕቀፉ ዝግጅት የተወሰደ ሌላኛው የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካች ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት የዋጋ ንረቱ በሁለት አሀዝ የሚለካ መሆኑ ለማክሮ-ኢኮኖሚው መረጋጋት ትልቅ ፈተና ሆኖ እንደቀጠለ ነው፡፡ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የዋጋ ንረቱን በያዘነው በጀት ዓመት ወደ ነጠላ አሃዝ ማውረድ አዳጋች እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል።
- የገቢ ዕቃዎች ዋጋ (Value of goods import) በ2017 በጀት ዓመት የ0.3 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ታሳቢ የተደረገ ሲሆን፣ በ2018 በጀት ዓመት የ5.5 በመቶ አማካይ ዕድገት እንደሚመዘገብ ትንበያው ያሳያል፡፡ ይህም ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ለሚሰበሰበው የመንግስት ገቢ ግምት መሰረት ነው፡፡
- ኢኮኖሚው ጦርነቱ ካደረሰው ጫና አንጻር ለማገገም የተወሰኑ ዓመታትን የሚጠይቅ በመሆኑ ቀድሞ በታቀደው ልክ የልማት ዕቅዶችን ለማስፈጸም ተግዳሮት መሆኑ አይቀርም፡፡ ከጦርነቱ ጋርም ተያይዞ የገጠመውን ከፍተኛ ወጪ ለመሸፈን ሲባል የተከሰተውን የፊሲካል ሚዛን መዛባት በመካከለኛ ዘመን ጊዜ ውስጥ የተመጣጠነ ለማድረግ የዕዳ ክፍያ ላይ ትኩረት ማድረግ የግድ የሚል ሲሆን፣ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ካለው የፋይናንስ ፍላጎት አንጻር የልማት ሥራዎች በተወሰነ ደረጃ መጓተት የሚያጋጥም በመሆኑ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ላይ ኡለታዊ ተጽእኖ የማሳደር ስጋት መኖሩን ግምት መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡

5.1.2 የፊሲካል ፖሊሲ ታሳቢዎች

መንግስት በሀገሪቱ የተከሰተውን የተዛባ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን ለማስተካከል ይረዳል ተብሎ የታመነበትን የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በተጠናከረ መንገድ ተግባራዊ በማድረጉ ተስፋ ሰጪ የኢኮኖሚ ለውጦች መታየት መጀምራቸውን መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ ሆኖም ከ2012 አጋማሽ ጀምሮ በሀገራችን የተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍል ተከስቶ የነበረው የአንበጣ መንጋ፣ ድርቅ እና የጎርፍ አደጋ፣ እንዲሁም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተከሰተው የህግ ማስከበር ጦርነትና ተያያዥ አለመረጋጋቶች በኢኮኖሚው ላይ ተደራራቢ ጫናዎችን ፈጥረዋል፡፡ ነገር ግን

ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ የተደረጉ መጠነ ሰፊ ማሻሻያዎች ኢኮኖሚው ይህ የደረሰበት ጫና ያስከተሉትን ተጽእኖዎች መቋቋም መቻሉን ግን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ጫና የበለጠ እየታየ ያለው ደግሞ በመንግስት የፊሲካል አቅም ላይ ነው፡፡ ጫናው ከመንግስት ገቢ አንጻር የታክስ ገቢ አሰባሰብ የተጠበቀውን ያህል አፈጻጸም እንዳያሳይ አድርጓል፡፡ እንዲሁም፣ የልማት አጋሮች የሚሰጡትን የልማት ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሱ ሲሆን፣ በተለይም በበጀት ድጋፍ መልክ የሚሰጡትን ድጋፍ ሙሉ ለሙሉ አቁመዋል፡፡ የ2017 በጀት ዋነኛ ዓላማ ባለፉት ዓመታት የተከሰቱት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቀውሶች እንዲሁም ቀደም ባሉ ዓመታት መንግስት የልማት ፕሮጀክቶቹን ፋይናንስ ለማድረግ የተከተለው አካሄድ ያስከተለውን የፊሲካል መዛባት በማስተካከል የፊሲካል ጤናማነትን እውን ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ በጀት በቅርቡ ስራ ላይ ከሚውለው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሁለት ኢላማዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን በዋናነትም አሁን የሚታየውን የተዳከመ የፊሲካል አቋም አስተማማኝ ደረጃ ላይ ማድረስ የሚቻለው አስተማማኝ ከሆነው የመንግስት ታክስ ገቢ ምንጭ የገቢ አሰባሰብ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ አማራጭ የሌለው መሆኑን ከግምት ተወስዷል፡፡ ለዚህም የታክስ ገቢ አሰባሰብ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሥራዎችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ ዋና የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የሁለተኛውን የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ለማስፈፀም የሚያግዘው የሦስት ዓመት ዝርዝር የፐብሊክ ኢንቨስትመንት ዕቅድ ጋር የወጪ ታሳቢዎቹ የተናበቡ እንዲሆኑ ተደረጓል፡፡ በአጠቃላይ ለበጀቱ ታሳቢ የተደረጉ የገቢና ወጪ ታሳቢዎች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

5.2 የፌዴራል መንግሥት የገቢ ታሳቢዎች

የፌዴራል መንግስት ገቢ ከሶስት ዋና ዋና ምንጮች የሚገኝ ሲሆን፣ እነዚህም የታክስ ገቢ፣ ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች እና የውጭ ዕርዳታ የገቢ ምንጮች ናቸው፡፡ በመሆኑም የ2017 በጀት ከነዚህ ምንጮች ሊገኝ የሚችለውን የፌዴራል መንግስት ገቢ ለማስላት የተለያዩ ታሳቢዎች የተወሰዱ ሲሆን፣ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- **የ2016 በጀት ዓመት የታክስ ገቢ ዕቅድ አፈጻጸም፡-** የፌዴራል መንግስት በ2016 በጀት ዓመት ከታክስ ምንጭ ብር 440.2 ቢሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዟል፡፡ በዚህም በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ የተሰበሰበው የተጣራ

የታክስ ገቢ ብር 313.9 ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህም የዓመታዊ ዕቅዱ 71.2 በመቶ መሰብሰቡን ያሳያል፡፡ ከዚህ በመነሳት በበጀት ዓመቱ ብር 33 ቢሊዮን የሚደርስ የታክስ ገቢ ላይሰበሰብ እንደሚችል ወይም የዓመታዊ ዕቅዱ 92.5 በመቶው (ብር 407.0 ቢሊዮን) ብቻ ሊሰበሰብ እንደሚችል ተገምቷል፡፡ በመሆኑም የ2016 የታክስ ገቢ አፈጻጸም ለ2017 የታክስ ገቢ ግምት እንደመነሻ ተወስዷል ፡፡

- **የክልሎች የጋራ ገቢ ድርሻ ከፍተኛ እየሆነ መምጣት በሚሰበሰበው የፌዴራል ገቢ ድርሻ ላይ የሚኖረው እንደምታ፦** በያዝነው በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በፌዴራል መንግስት ተሰብስቦ ለክልሎች የተላለፈው የጋራ ገቢ ድርሻ ብር 54.3 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን፣ ይህም በ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ተሰብስቦ ከተላለፈው አንጻር በ29 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህም ከፌዴራል መንግስት የሚታጣው የገቢ ድርሻ ከተጠበቀው በላይ በመሆኑ የፌዴራል መንግስት ገቢ እየቀነሰ መሄዱን ያሳያል፡፡ ስለሆነም ይህ እውነታ የቀጣዮቹ ዓመታት የፌዴራል መንግስት የታክስ ገቢ ግምት ሲዘጋጅ ታሳቢ ተደርጓል፡፡
- **የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች ለታክስ ገቢ ትንበያ ያላቸው እንደምታ፦** ከላይ የተገለጹት የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎችና ሊኖር የሚችለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለታክስ ገቢ አቅም በየታክስ ዓይነቱ (የቀጥታ ግብርና ታክስ፣ የአገር ውስጥ ኤክሳይዝና ተጨማሪ እሴት ታክሶችና የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ፣ ኤክሳይዝ፣ ተ.እ.ታ. እና ሱር ታክሶች) የሚኖራቸው እንደምታ በዝርዝር በትንበያ ሞዴሉ እንደዋነኛ ታሳቢ ተደርጓል፣
- **የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያ ታሳቢዎች፦** ከያዝነው በጀት ዓመት ጀምሮ ለፓርላማ ቀርበው እንደሚጸድቁና ሥራ ላይ እንደሚውሉ የሚጠበቁ የታክስ ህጎች በቀጣዮቹ በጀት ዓመታት ለታክስ ገቢ አሰባሰቡ የሚኖራቸውን ተጨማሪ አቅም ከግምት ውስጥ ገብቷል። እነዚህን የታክስ ህግ ማሻሻዎች ተግባራዊ በማድረግ በ2017 በጀት ዓመት ብር 92.5 ቢሊዮን ተጨማሪ የታክስ ገቢ መሰብሰብ ይቻላል የሚል ግምት ተወስዷል፡፡ በቀጣዮቹ ዓመታት ማሻሻያዎቹን የበለጠ አጠናክሮ ተግባራዊ በማድረግም የበለጠ የታክስ ገቢ መሰብሰብ እንደሚቻል በማሰብ የተለጠጠ ዕቅድ ተይዟል፡፡ በመሆኑም እነዚህን በሥራ ላይ ለማዋል የታቀዱት ዋና ዋና የታክስ ህጎች እንደሚከተሉት ቀርቧል፣
    - **የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ፡-** ማሻሻያዉ ከተ.እ.ታ ነጻ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶችን በጥናት ላይ በመመርኮዝ ወደ ሥርዓቱ እንዲገቡ

በማድረግ፣ የተ.እ.ታ መመዝገቢያ ጣሪያውን በማሻሻል፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የታክስ አከፋፈሉን ሂደቱን በማቃለል የተሻለ ገቢ እንደሚሰበሰብ ታሳቢ ተደርጓል። በተጫማሪም ማሻሻያዉ በተለይ ኢ-ኮመርስን ወደ ስርዓቱ በማስገባት ገቢውን እንደሚጨምር ታሳቢ ተደርጓል፡፡

- **ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፡-** ይህ ማሻሻያ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በቅንጦት ዕቃዎች እንዲሁም ለጤና ጥሩ ያልሆኑ ምርቶች ፍጆታ በመቀነስ በጤና ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋ እንደሚቀንስ ይጠበቃል፡፡ በቅርብ ዓመታት ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻያዎች የተደረጉ ቢሆንም አሁንም ካለው ተለዋዋጭ የኢኮኖሚ ሁኔታ ማሻሻል አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም ሶስት የኤክሳይዝ ታክስ ዕርከኖች ላይ ማሻሻያ የሚደረግ ሲሆን ይሄውም፤ በ2016 እና በ2017 በጀት ዓመታት ሁለቱ ይተገበራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በተወሰኑ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች ላይ (ለምሳሌ አልኮልና የአልኮል ምርቶች) ማሻሻያ የሚደረግባቸው ይሆናል፡፡ በመሆኑም የታክስ አሰባበሰቡ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ታሳቢ ተደርጓል።
- **የኤክሳይዝ ቴምብር፡-** የኤክሳይዝ ቴምብር የጨረታ መስፈርቶች ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ጨረታው ተጠናቅቆ ስርዓቱ በ2016 በጀት ዓመት ተግባራዊ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ኤክሳይዝ የተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰብ ገቢ ተግባራዊ ሲደረግ ህገ-ወጥ ንግድን በማስቀረት ወይም በመቀነስ (በተለይ በሲጋራ እና አልኮልና የአልኮል ውጤቶች ላይ) ይህ ስርዓት በሚዘረጋበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ ገቢ ለገቢ አሰባሰቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

- **የገቢ ግብር ማሻሻያ፦** የግብር ነፃ እና እፎይታን በመቀነስ፣ የዝቅተኛ ተለዋጭ ታክስ እርከን ሥርዓትን በመዘርጋት እና የታክስ ቀንሶ ማስቀረት ሥርዓትን በማሻሻል ተጨማሪ ገቢ ሊገኝ እንደሚችል ታሳቢ ተደርጓል።

- **የታክስ ማበረታቻ ማሻሻያ፦** ከአላማው ውጭ እንዳይውል ጠንካራ ሥርዓት በመዘርጋትና የሚታጣውን የመንግስት ገቢ ለመቀነስ እንዲቻል አገልግሎቱ በማዕከል በገንዘብ ሚኒስቴር ብቻ እንዲሆን በማድረግ ጠንካራ ስራ

ተሰርቷል፡፡ በቀጣይ ዓመት ይኸው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታሳቢ ተደርጓል።

- **አረንጓዴ (የተሽከርካሪ ዝውውር አመታዊ) ታክስ**፡- አሁን ያለው ሥርዓት የሚፈለገውን ገቢ ከማስገኘት እና የአካባቢ ብክለት ችግርን ከመቀረፍ አንጻር በቂ ባለመሆኑ፤ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ዝውውር ታክስ እንደሚጀመር ታሳቢ ተደርጓል።

- **የንብረት ታክስ** (Property Tax) **ህግ**፡- ታክሱን የመሰብሰብ ሥልጣን በሚመለከት የፌዴሬሽን እና የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶች በጋራ የንብረት ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን ለክልሎች እና ለከተማ አስተዳደሮች መስጠታቸውን ተከትሎ ረቂቅ የንብረት ታክስ አዋጁ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ውይይት ተደርጎበት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ከዚህ ታክስ የሚገኘው ገቢ የክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮችን ገቢ እንደሚጨምር ይጠበቃል:: ይህም የታክስ መሰረቱን በመስፋት የክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮች የታክስ ገቢን እንደሚጨምር ግምት ተወስዷል።

- **ታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች**፡- የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት የሰው ሀይልና ተቋማዊ አቅምና የአሠራር ችግሮችን እና አደረጃጀቱን በጥልቀት በመፈተሽ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን፣ ለዚህም በተግባር ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ በመንግስት በኩል ቁርጠኝነት እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል፡፡ አብዛኛዉ ታክስ ከፋይ በፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንዲከፍል በማድረግ፣ በአንጻራዊነት የታክስ ሰብሳቢዎች ትኩረት ታክስን በፍላጎት በማይከፍሉ ታክስ ከፋዮች ላይ ብቻ እንዲሆን እና የታክስ ባለሙያዎች ታክስን በፍላጎት ላይ ተመስርቶ እዲከፍሉ በሚያደርጉ አገልግሎት ተኮር የአመለካከት ለዉጥ በሚያመጡ ትምህርቶችና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ላይ እንዲሆን፤ እንዲሁም በታክስ አዲትና ቀጣይነት በለዉ ሁኔታ ታክስ በማይከፍሉት ላይ እንዲሆን ማድረግ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ነገር ግን ግብርና ታክስ የማይከፍሉ የተለያዩ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዘርፍ

ውስጥ የሚሳተፉ የኢኮኖሚ ተዋናዮችን በግብር ሥርዓቱ ማስገባት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ማሻሻያ ማካሄድ አስፈላጊ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጓል።

5.2.1 ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች ታሳቢዎች

በቀጣዮቹ ዓመታት ታክስ ካልሆኑ ምንጮች የሚሰበሰቡት ገቢዎች በዋናነት ከመንግስት የልማት ድርጅቶችና ከሌሎች ተቋማት ከሚገኘው የዘቀጠ ትርፍና የትርፍ ድርሻ ገቢ፣ በባለበጀት መ/ቤቶች ከሚሰጡ አገልግሎቶች ክፍያ፣ ከመንግስት ዕቃዎች ሽያጭ እና ከመሳሰሉት ከሚገኙ ገቢዎች ነው። በቀጣዮቹ ዓመታት ትልልቅ ገቢዎች ከሚሰበሰብባቸው ምንጮች ሊገኙ የሚችለው ገቢ መጠንን የሚያሳይ ግምት መረጃ ከየተቋማቱ የተገኘ ሲሆን፣ ከበርካታ ተቋማት የሚሰበሰቡ ጥቃቅን ገቢዎችን ደግሞ ባለፉት ዓመታት የተሰበሰበውን ገቢ መረጃ በመጠቀም (trend forecast) ለመገመት ተሞክሯል።

5.2.2 የውጭ ዕርዳታና ብድር (soft loan) ዋና ዋና ታሳቢዎች

የውጭ ሀብት ከፕሮጀክቶች ዕርዳታና ብድር እንዲሁም በቀጥታ ወደ ትሬዠሪ ከሚፈሱ ፕሮግራሞች የሚገኝ የዕርዳታ እና ብድር ሀብት ነው። በበጀት ውስጥ የተካተቱ የብድር ሀብቶች በረዥም ጊዜ የሚከፈሉ እንዲሁም ዝቅተኛ ወለድ እና ረጅም የመክፈያ ችሮታ ጊዜ ያላቸው የብድር ዓይነቶች ናቸው። ከፕሮጀክቶች ዕርዳታና ብድር የሚገኙት ገቢዎች በቀጥታ ለፕሮጀክቶቹ ማስፈጸሚያ ብቻ የሚውሉ ሲሆን ከአስፈጻሚ አካላት በተገኘ የፕሮጀክቶች ዝርዝር መሠረት የተገመተ ነው። በአንጻሩ ወደ ትሬዠሪ በቀጥታ የሚፈሱት የብድርና ዕርዳታ ገቢዎች በልማት አጋሮች እና በመንግስት በተደረሱ ስምምነቶች መሠረት እንዲሁም፣ የፍሰት ታሪካቸውን በመገምገም የተገመተ ነው። ነገር ግን ከልማት አጋሮች የሚገኘው የገቢ ግምት ምንም እንኳን ስምምነትን መሠረት ያደረገ ቢሆንም፣ ባለፉት ሶስት ዓመታት ከሰሜኑ የሀገራችን የሰላም ማስከበር ዘመቻ ጋር ተያይዞ ብድርና ዕርዳታ የቀነሰ መሆኑ ይታወቃል። ሆኖም በያዝነው በጀት ዓመት በተደረሰው የሰላም ስምምነት ተከትሎ ከልማት አጋሮች እየተገኙ ያሉ ምላሾች ጥሩ የሚባሉ በመሆኑ በቀጣይነትም ክትትል በማድረግ ከዚህ አንጻር ሊካተቱ የሚችል የውጭ ሀብት እንዲካተትና ለልማት ፋይናንሲንግ እንዲውል የሚደረግ ይሆናል። ይሁን እንጂ በ2016 የገቢ ታሳቢዎች ውስጥ ከልማት አጋራት የበጀት ድጋፍ እንደሚገኝ ታሳቢ አልተደረገም።

ሠንጠረዥ 3፡- የ2017 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት የገቢ ዕቅድ (በሚሊዮን ብር)

የገቢ ዓይነት	2016		የ2017 የገቢ ዕቅድ	ዕድገት በመቶኛ	
	በጀት	ግምት		ከ2016 በጀት	ከ2016 ግምት
ጠቅላላ ገቢና ዕርዳታ	**520,606.43**	**477,409.14**	**612,697.56**	**17.69**	**28.34**
የአገር ውስጥ ገቢ	**479,486.79**	**446,590.30**	**563,605.60**	**17.54**	**26.2**
የታክስ ገቢ ድምር	**440,825.68**	**407,929.19**	**502,036.23**	**13.89**	**23.1**
ቀጥታ ታክሶች	**141,481.45**	**140,540.70**	**161,126.77**	**13.89**	**14.6**
የአገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች	**111,755.49**	**103,760.88**	**127,273.22**	**13.89**	**22.7**
የሀገር ውስጥ ዕቃዎች ተ.እ.ታ	39,688.02	36,848.87	46,198.87	**16.41**	**25.4**
የአገልግሎት ተ.እ.ታ	48,630.62	45,151.75	54,383.19	**11.83**	**20.4**
የዕቃዎች ኤክሳይዝ ታክስ	21,450.10	19,915.63	24,428.54	**13.89**	**22.7**
ተርን ኦቨር ታክስ	121.70	113.00	138.60	**13.89**	**22.7**
የቴምብር ሽያጭ ቀረጥ	1,865.05	1,731.63	2,124.02	**13.89**	**22.7**
የውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ	**187,588.74**	**163,627.61**	**213,636.24**	**13.89**	**30.6**
የጉምሩክ ቀረጥ /የገቢ ዕቃዎች/	67,838.26	59,177.03	86,657.89	**27.74**	**46.4**
የገቢ ዕቃዎች ኤክሣይዝ ታክስ	16,740.92	14,603.53	19,065.47	**13.89**	**30.6**
የገቢ ዕቃዎች ተ.እ.ታ	69,849.25	60,931.27	79,548.12	**13.89**	**30.6**
ሱር ታክስ	33,147.93	28,915.78	28,350.67	**-14.47**	**-2.0**
ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች	**38,661.11**	**38,661.11**	**61,569.37**	**59.25**	**59.3**
ጠቅላላ የውጭ ዕርዳታ	**41,119.64**	**30,818.83**	**49,091.96**	**19.39**	**59.29**
የመሠረታዊ አገልግሎት ክለላ ድጋፍ	6,349.42	0.00	7,292.38	**14.85**	**0.0**
የፕሮጀክቶች ዕርዳታ	34,770.22	30,818.83	41,799.58	**20.22**	**35.63**

5.3 የፌዴራል መንግስት ወጪ

በሀገራችን ካለው ከፍተኛ የልማት ፍላጎት አንጻር ክፍተት እንደመኖሩ መጠን የፌደራል መንግስት የወጪ ፍላጎት ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም፣ የሚኖረውን ውስን የመንግስት ሀብት አሁን ከተፈጠረው የፊሲካል ጫና አንጻር ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው ለሚገቡ የወጪ ፍላጎቶች ማዋል አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንጻር የመንግስትን የወጪ ጣሪያ ለመወሰን መንግስት የሚከተለውን የወጪ ፖሊሲ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና ሊኖር የሚችለውን የፋይናንስ አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ይዘጋጃል።

በመሆኑም የፌደራል መንግስት የገቢ ሀብት ትንበያን መሠረት በማድረግ ለፌደራል መንግስት መደበኛና ካፒታል ወጪዎች እንዲሁም ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የበጀት

ድጋፍ እና የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ የሚያስፈልገው ወጪ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

5.3.1 የፌዴራል መንግስት መደበኛ ወጪ

የመደበኛ ወጪ መንግስት ለሚከተለው ጤናማ የፊሲካል ጤናማነትን ማስፈን የፖሊሲ አቅጣጫ አብዛኛው ለዕዳ ክፍያ የሚውል ሲሆን በጦርነቱ የወደሙ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞው ይዘታቸው ለመመለስ የመልሶ ማቋቋም ስራን ታሳቢ አድርገዋል።

በዚህም መሰረት ለ2017 በጀት ዓመት ብር 971.2 ቢሊዮን የተመደበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 451.3 ቢሊዮን (46.5 በመቶ) ለፌዴራል መንግስት የመደበኛ ወጪ ተደግፎ የቀረበ ሲሆን ከ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው ብር 370.1 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር 81.2 ቢሊዮን ወይም በ21.9 በመቶ ዕድገት ያሳያል። በመደበኛ ወጪ ከተደገፈው ውስጥ ለዕዳና ሃብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን ካፒታል ማሳደጊያ የሚውል ብር 30 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል።

5.3.2 የፌዴራል መንግስት ካፒታል ወጪ

የፌዴራል መንግስት የካፒታል ወጪ የሚሸፈነው ከአገር ውስጥ ከመንግስት ግምጃ ቤት እና ከመ/ቤቶች የውስጥ ገቢ እንዲሁም ከውጪ ብድርና ዕርዳታ ነው። የ2017 በጀት ዓመት ከመንግስት የትኩረት አቅጣጫ አንጻር በመካሄድ ላይ ላሉ ነባር ፕሮጀክቶች አሁን ያለውን ዕቅድ ለማሳካትና እንዲጠናቀቁ ለማድረግ እና በግጭቱ ምክንያት የወደሙ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞው ይዘታቸው ለመመለስ ለመልሶ ማቋቋም ቅድሚያ በመስጠት በሶስት ዓመቱ ልማት ኢንቨስትመንት ዕቅድ መሰረት የዘላቂ ልማትን፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ የኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት ማስፋፋት፣ የግብርና ምርታማነት፣ የመስኖ ልማት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ግቦችን ለማሳካት እንዲያስችሉ ለተጀመሩ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ እንዲጣጣም ተደርጎ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም ለ2017 የፌደራል መንግስት የካፒታል ወጪ ውስጥ ብር 215.4 ቢሊዮን ወይም 76 በመቶ ከመንግስት ግምጃ ቤት፤ ከውጭ እርዳታ ብር 39.8 ቢሊዮን እና ከውጭ ብድር ብር 26.9 ቢሊዮን በድምሩ ብር 283.1 ቢሊዮን እንደሚሆን ታቅዷል። ይህም በ2016 በጀት ዓመት ከተፈቀደው ብር 203.4

ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር በብር 79.7 ቢሊዮን ወይም በ39.2 በመቶ ጭማሪ እንዳለው ያሳያል፡፡

5.3.3 የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ

የክልል መንግስታት የበጀት ድጋፍ የክልላዊ መንግስታት አብዛኛው ወጪ የሚሸፈነው ከፌዴራል መንግስት በሚተላለፍ የበጀት ድጋፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም መንግስት በክልሎች ለሚከናወኑት የገጠር መሰረተ ልማት፣ የአቅም ግንባታ እንዲሁም ድህነት ተኮር የወጪ ዘርፎች ትኩረት የሰጠ ነው፡፡ ለ2017 በጀት ዓመት ለክልልላዊ መንግስታት 222.7 ቢሊዮን የተደገፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከመንግስት ግምጃ ቤት የተመደበው ብር 215.3 ቢሊዮን ሆኗል፡፡ በመሆኑም የ2017 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት የተደገፈው የበጀት ድጋፍ ከ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው ጋር ሲነጻጸር 5 በመቶ ጭማሪ እንዳለው ያሳያል፡፡ የ2017 በጀት ዓመት ጠቅላላ የክልሎች ድጋፍ ከሁሉም የፋይናንስ ምንጭ ለ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው ብር 214.1 ቢሊዮን ጋር ሲታይ በብር 8.6 ቢሊዮን ወይም በ4 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡

5.3.4 የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ

የዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ የዘላቂ የልማት ግቦችን ማሳካት እንዲቻል በክልሎች ለሚካሄዱ ዘላቂ ልማትና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የአግሮ ፕሮሰሲንግ እና ለስራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም በክልሎች ለሚካሄዱ ለአነስተኛ እና መካከለኛ መስኖ ልማት የካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 14.0 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡ ከዚህ በላይ ቀጥሎ የበጀት ዝግጅቱ ታሳቢዎችና ማብራሪያዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6. የ2017 ፕሮግራም በጀት አዘገጃጀትና ድጋፍ

የፌዴራል መንግሥት የ2017 በጀት ዓመት የበጀት ዝግጅት የአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ አካል የሆነውን የ2016 - 2018 የልማትና ኢንቨስትመንት እቅድ የተቀመጡ ግቦችን ከማስፈጸም አኳያ፣ የሀገር ደህንነት ከማስጠበቅ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጐችን ከመርዳት እና በጦርነቱ የወደሙ መሰረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች መልሶ ከማቋቋም እንዲሁም በቀጣይ ሊኖር የሚችለውን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫዎችና ዓላማዎች እና የ2017-2021 የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ማዕቀፍን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የአምስተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት አካል የሆነው (2017-2018) በጀት ዝግጅት የ2016 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም መነሻ በማድረግ በፕሮግራሙ ዘመኑ መጨረሻ የታቀዱትን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት በመንግስት የተቀመጡ ግቦችን ከማሳካት አንፃር፣ ከመንግሥት የፋይናንስ አቅም፣ መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ተልዕኮና ማንዴት አኳያ ለውጤቶች፣ ለዋና ዋና ተግባራትና ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን ወጪ በመገምገም በጀቱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ለፕሮግራም በጀት ዝግጅት እንዲረዳ አመልካች የበጀት ጣሪያ ከዝርዝር መመሪያ ጋር እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ በበጀት ጥሪው መሠረት አስፈጻሚ መ/ቤቶች የበጀት ጥያቄቸውን አቅርበው ከስራ ፀባያቸው አኳያ ከመ/ቤቶች ጋር የበጀት ስሚ ተከናውኗል፡፡

6.1. የ2017 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ዋና ዋና ታሳቢዎች

6.1.1. ጠቅላላ ታሳቢዎች

የፕሮግራም በጀት በጀትን ከውጤት ጋር የሚያዛምድ የበጀት አሰራር ስርዓት ሲሆን፣ ውጤትን ለመለካት፣ ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ እቅድን ከበጀት ጋር ለማስተሳሰር እና የመደበኛና የካፒታል ወጪዎችን ለማቀናጀት የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ ለ2017 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ታሳቢ የተደረጉ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ለ2017 በጀት ዓመት የተዘጋጀው በጀት የአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ አካል የሆነውን የ2016-2018 የልማትና ኢንቨስትመንት እቅድ እና

የፕሮግራም በጀት በማጣጣም የተቀመጡ ግቦችና አቅጣጫዎችን ከማስፈጸም አኳያ እና ሊኖር የሚችለውን የሀብት መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

- በዕቅዱ ዘመን ለማህበራዊና ለኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ ለኢንዱስትሪ ልማትና ለኤክስፖርት መስፋፋት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ፣ ለመስኖ ልማት እና ለግብርና ልማት የተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት በቀጣይም ትኩረት እንደሚሰጠው ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

- በካፒታል ወጪ በመካሄድ ላይ ላሉ ነባር ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠት እና በውጭ ፋይናንስ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ደግሞ የመንግስት ድርሻን ታሳቢ በማድረግ፣

- የሀገር ደህንነት ለማስጠበቅ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት ለተጐዱ ዜጐች የእለት እርዳታ ለማቅረብ እና ለልማታዊ ሴፍቲኔት የሚያስፈልገውን ወጪ ታሳቢ በማድረግ፣

- በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ መሰረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞ ይዞታቸው ለመመለስ የመልሶ ማቋቋም ስራን ታሳቢ በማድረግ፣

- ሊኖር የሚችለውን የአገር ውስጥ ብድር ጫና ግምት ውስጥ በማስገባት ለአገር ውስጥ እዳ ክፍያ እንዲሁም የውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ በክልሎች በተጓዳኝ ፋይናንስ /Matching Fund/ ጭምር ለሚካሄዱ አነስተኛ እና መካከለኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች እና ለነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት፣

- መ/ቤቶች በተመደበላቸው በጀት የሚያከናውኑት የመሰረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ለህብረተሰቡ የሚያስገኙት ውጤቶችና ለውጦችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- የመንግስት መ/ቤቶች የቀረጿቸው ፕሮግራሞች ከየመ/ቤቱ ተልዕኮና ማንዴት ጋር የተጣጣሙ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ፤

- መ/ቤቶች ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጧቸውን አላማዎች እና ፕሮግራሞች በቅደም ተከተል እንዳቀረቡ ታሳቢ በማድረግ፤

- የፕሮግራም በጀት በቁጠባ፣ በብቃትና በውጤታማነት እንደሚመራና እንደሚተገበር ታሳቢ በማድረግ፣

- በአጠቃላይ በመደበኛ ወጪ ሊያሰራ የሚችል በጀት እና በካፒታል ወጪ ደግሞ ለፕሮጀክቶች ከፊዚካል ስራው ጋር የተጣጣመ በጀት በመመደብ በቀጣይ በጀት አመት ከመጠባበቂያ በጀት ተጨማሪ በጀት እንደማይኖር ታሳቢ በማድረግ፣

የአምስተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት አካል የሆነው /2017-2018/ የፕሮግራም በጀት መ/ቤቶች ካስቀመጡት ስትራቴጂክ ዓላማ፣ ግቦች፣ ከሚጠበቁ ውጤቶች እና ከ2016 የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም አኳያ በመገምገም የ2017 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ተዘጋጅቷል።

6.1.2. የመደበኛ ወጪ ታሳቢዎች

- መ/ቤቶች የተሰጣቸውን ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችላቸው በመደበኛ ወጪ ቁጠባና ለብክነት የተጋለጡ ወጪዎችን መቀነስ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀጣይ በጀት አመት ሊያሰራ የሚችል በጀት በመመደብ ከመጠባበቂያ በጀት ተጨማሪ በጀት እንደማይኖር ታሳቢ በማድረግ፣

- ከልማታዊ ሴፍቲኔት ውጪ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ለዜጐች የዕለት ዕለት ደራሽ ዕርዳታ ለማቅረብ የሚያስፈልገውን በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ በመደበኛ በጀት የሚያስከትለውን የወጪ ግምት ታሳቢ በማድረግ፣

- በአለም ገበያ የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ የተፈጠረውን የዋጋ ልዩነት ለመሸፈን የድጐማ በጀትን ታሳቢ በማድረግ፣

- ከመ/ቤቶች የሚጠበቀው ውጤት እና ከሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት አኳያ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የግብዓት ወጪዎች በማስላት፣

- የመ/ቤቶችን የበጀት አጠቃቀም፣ የዋጋ ንረት እንዲሁም በመንግስት ተመን የወጣላቸውን /ምግብ፣ የውሎ አበል፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ወዘተ.../ መሰረት በማድረግ፣

- ከመንግስት ግምጃ ቤት ለሚገዙ መሳሪያዎች፣ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የቀረጥ ሂሳብ በእያንዳንዱ መ/ቤት እንዲያዝ በማድረግ፣

6.1.3. የካፒታል ወጪ ታሳቢዎች

- ከሶስት ዓመቱ የልማት እና ኢንቨስትመንት ዕቅድ አኳያ የዘላቂ ልማት ዘርፎች እና የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ የኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት ማስፋፋት፣ የግብርና ምርታማነትን፣ የመስኖ ልማት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ግቦችን ለማሳካት እንዲያስችል ለተጀመሩ የካፒታል ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠት ከፊዚካል ስራው ጋር የተጣጣመ በጀት እንዲመደብ በማድረግ፣

- በዩኒቨርሲቲዎች ያሉ ፕሮጀክቶች በርካታ ከመሆናቸውም በላይ እነዚህን ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው በጀት ከመንግስት የፋይናንስ አቅም በላይ በመሆኑ ፕሮጀክቶቹን እንደገና ከዩኒቨርሲቲዎች ሪፎርም እና አግባብነት አኳያ በመገምገም የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በቀጣይ በጀት አመት ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች አስፈላጊው በጀት እንዲመደብ በማድረግ፣

- በውጭ ፋይናንስ ጭምር ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች የውጭ ፋይናንስ ፍሰት በእርግጠኝነት በበጀት ዓመቱ ሊፈስ የሚችለውን የገንዘብ መጠን በበጀት እንዲያዝ በማድረግ፣

- በውጭ ፋይናንስ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ከመንግስት የሚያስፈልገውን ተጓዳኝ ፋይናንስ (Matching Fund) እንዲያዝ በማድረግ፣

- በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ መሰረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞ ይዞታቸው ለመመለስ የመልሶ ማቋቋም ስራን ታሳቢ በማድረግ፣

- አስፈጻሚ መ/ቤቶች ለፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጡና ፕሮጀክቶች በታቀደው ወጪ፣ ጊዜና ጥራት እንዲካሄዱ በማድረግ የሀብት ብክነት እንደማይኖር ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የመ/ቤቶች የቢሮ ኪራይ ወጪ ለመቀነስ እና ምቹ የሥራ ሁኔታን ለማመቻቸት በ2017 በጀት ዓመትም የመንግስት ቢሮዎች ግንባታ በማዕከል በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እንደሚካሄድ ታሳቢ ተደርጎ በጀቱ ተደግፏል።

በአጠቃላይ የ2017 በጀት አመት የበጀት ዝግጅት ከፍ ብለው የተመለከቱትን ታሳቢዎችና አቅጣጫዎች ግምት ውስጥ ያስገባና ያስቀመጠ ሲሆን ከመንግሥት የሚመደበው የበጀት ድጋፍም በመደበኛና በካፒታል ወጪዎች በመለየት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

6.2. ጠቅላላ በጀት

ለ2016 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ብር 370.13 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ብር 203.44 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 214.07 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14.00 ቢሊዮን በአጠቃላይ ብር 801.65 ቢሊዮን መፈቀዱ ይታወሳል።

ለ2017 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ብር 451.31 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ብር 283.20 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 222.70 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14.0 ቢሊዮን በጠቅላላው 971.2 ቢሊዮን ብር ተደግፏል። በዚህም


መሠረት የፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ የ2017 በጀት ለ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት በብር 169.56 ቢሊዮን ወይም የ 21.1 በመቶ ዕድገት ያሳያል።

የ2017 በጀት ዓመት የበጀት ድጋፍ

በቢሊዮን

የወጪ አይነት	የ2016 የጸደቀ በጀት	የ2017 የተደገፈ በጀት	ልዩነት	
			በመጠን	በ%
1	2	3	4=3-2	5=4/2
መደበኛ	370.14	451.31	81.17	21.93
ካፒታል	203.44	283.19	79.76	39.21
ክልል ድጋፍ	214.07	222.70	8.63	4.03
የዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ (SDGs)	14.00	14.00	0.00	0.00
ድምር	801.65	971.20	169.56	21.15

ከሠንጠረዡ ላይ መረዳት እንደሚቻለው ለ2017 ከተደገፈው በጀት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ የሚገኘው ለመደበኛ ወጪ የተመደበው በጀት ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ የተደገፈው ደግሞ ለካፒታል ወጪ ነው።



የበጀት ድጋፉና ድልድሉ በዋና ዋና ወጪዎች ይህን ሲመስል፣ ለመደበኛና ለካፒታል ወጪዎች የተመደበውን በጀት በዘርፍ በመለየት ከዚህ በታች በአጭሩ ለማብራራት ተሞክሯል::

6.2.1 የመደበኛ ወጪ


የ2017 በጀት ዓመት የመደበኛ ወጪ ብር 451.31 ቢሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ብር 106.85 ቢሊዮን (23.67%)፣ ለኢኮኖሚ አገልግሎት ብር 8.47 ቢሊዮን (1.88%)፣ ለማኅበራዊ አገልግሎት ብር 68.19 ቢሊዮን (15.11%) እና ለሌሎች ክፍያዎች ብር 267.80 ቢሊዮን (59.34%) ነው:: ከሌሎች ክፍያ ውስጥ ደግሞ ለዕዳ ክፍያ ብር 139.31 ቢሊዮን (52.0%) እና ለመጠ ባበቂያ ብር 81.46 ቢሊዮን (30.4%) የተመደበ ነው::

በአጠቃላይ የ2017 በጀት ዓመት መደበኛ ወጪ በ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 370.13 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር በብር 81.17 ቢሊዮን ወይም የ 21.93 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

የ2017 በጀት ዓመት መደበኛ ወጪ

በቢሊዮን ብር

አገልግሎት	የ2016 የጸደቀ በጀት	የ2017 በጀት		ልዩነት		ድርሻ በመቶኛ
		የተጠየቀ	የተደገፈ	በመጠን	በ%	
1	2	3	4	5=4-2	6=5/2	
አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት	80.61	118.06	106.85	26.24	32.55	23.68
ኢኮኖሚ	6.90	10.07	8.47	1.57	22.75	1.88
ማህበራዊ	54.23	84.61	68.19	13.96	25.74	15.11
ሌሎች	228.40	282.35	267.80	39.40	17.25	59.34
የበጀት ድጋፍ	21.00	46.03	47.03	26.03	123.95	
ዕዳ ክፍያ	159.20	139.31	139.31	-19.89	-12.49	
መጠባበቂያ	47.30	96.01	81.46	34.16	72.22	
ድምር	370.14	495.09	451.31	81.17	21.93	



6.2.1.1 አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ

በ2017 በጀት ዓመት የተደገፈው በጀት ብር 106.85 ቢሊዮን ሲሆን፣ ከ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 80.61 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 26.24 ቢሊዮን ወይም 32.55 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ይህም ሊሆን የቻለው ለሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ፣ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ለጉምሩክ ኮሚሽን፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ለገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ፣ ለኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ፣ ለፍትህ ሚኒስቴር እና ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ተጨማሪ የበጀት ድጋፍ በመደረጉ ነው።

6.2.1.2 ኢኮኖሚ ዘርፍ

በኢኮኖሚ ዘርፍ በ2017 በጀት ዓመት የተደገፈው መደበኛ ወጪ ብር 8.47 ቢሊዮን ሲሆን ለ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 6.9 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 1.57 ቢሊዮን ወይም በ 22.75 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ይህም ሊሆን የቻለው ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን፣ ለግብርና ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ

ልማት ኢንስቲትዩት እና ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጨማሪ የበጀት ድጋፍ በመደረጉ ነው።።

6.2.1.3 ማኅበራዊ ዘርፍ

ለማኅበራዊ ዘርፍ ለ2017 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 68.19 ቢሊዮን ሲሆን፣ ለ2016 በጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት ብር 54.23 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 13.96 ቢሊዮን ወይም የ 25.74 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ለጭማሪው ዋናው ምክንያት ለአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ፣ የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ፣ ለቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ፣ ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት፣ ለአዲስ አበባ ፣ ለጎንደር ፣ ለመቀሌ እና ለአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲዎች ተጨማሪ የበጀት ድጋፍ በመደረጉ ነው።

6.2.1.4. ሌሎች

ለሌሎች አገልግሎቶች ለ2017 በጀት ዓመት ብር 267.80 ቢሊዮን የተደገፈ ሲሆን ለዕዳ ክፍያ 52.0 በመቶ ፣ ለመጠባበቂያ በጀት 30.4 በመቶ እና ለበጀት ድጋፍ 17.6 በመቶ እንዲሆን የተደገፈ ነው። በመሆኑም ብር 139.31 ቢሊዮን ለዕዳ ክፍያ፣ ብር 81.46 ቢሊዮን ለመጠባበቂያ እንዲሁም ብር 47.03 ቢሊዮን ለበጀት ድጋፍ የተደገፈ ነው።


6.2.1.5 መደበኛ ወጪ በኢኮኖሚ ጠቀሜታ

የ2017 በጀት ዓመት ጠቅላላ የመደበኛ ወጪ በኢኮኖሚ ጠቀሜታ ሲታይ ብር 127.18 ቢሊዮን ወይም 28.18 በመቶ ለደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና ብር 324.13 ቢሊዮን ወይም 71.82 በመቶ ለስራ ማስኬጃ የተደገፈ ነው። ለ2017 በጀት ዓመት ለደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች የተደገፈው ለ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው ብር 67.45 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር የብር 59.73 ቢሊዮን ወይም የ88.55 % እንዲሁም ለሥራ ማስኬጃ ወጪ ለ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 302.68 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 21.45 ቢሊዮን ወይም የ 7.09 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

የ2017 እና የ2016 የመደበኛ ወጪ የደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና የሥራ ማስኬጃ በጀት ንጽጽር

በቢሊዮን ብር

አገልግሎት	የ2017 በጀት አመት			የ2016 የጸደቀ በጀት			ልዩነት			
							ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች		ሥራ ማስኬጃ	
	ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች	ሥራ ማስኬጃ	ድምር	ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች	ሥራ ማስኬጃ	ድምር	መጠን	%	መጠን	%
አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት	46.28	60.57	106.85	33.10	47.51	80.61	13.18	39.82	13.06	27.49
ኢኮኖሚ	3.20	5.27	8.47	2.75	4.14	6.89	0.45	16.36	1.13	27.29
ማህበራዊ	26.70	41.49	68.19	22.60	31.64	54.24	4.10	18.14	9.85	31.13
ሌሎች	51.00	216.80	267.80	9.00	219.39	228.39	42.00	466.67	-2.59	-1.18
ድምር	127.18	324.13	451.31	67.45	302.68	370.13	59.73	88.55	21.45	7.09



6.2.2 የካፒታል ወጪ

የ2017 በጀት ዓመት ጠቅላላ የካፒታል ወጪ ብር 283.2 ቢሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 215.45 ቢሊዮን ከአገር ውስጥ ምንጭ፣ ብር 39.84 ቢሊዮን ከውጭ እርዳታ እና ብር 26.88 ቢሊዮን ከውጭ ብድር የሚሸፈን ነው። ጠቅላላ ለካፒታል የተያዘው በጀት ለ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ከብር 203.44 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 79.76 ቢሊዮን ወይም 39.20 በመቶ ጭማሪ ያሳያል።


የ2017 በጀት ዓመት የካፒታል ወጪ ከ2016 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር ለአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ ብር 11.93 ቢሊዮን፣ ለኢኮኖሚ ዘርፍ ብር 34.44 ቢሊዮን፣ ለማህበራዊ ዘርፍ ብር 28.67 ቢሊዮን እና ለሌሎች ዘርፍ ብር 4.72 ሊዮን ጭማሪ በማድረግ ተደግፏል። የ2017 የካፒታል ወጪ ከ2016 በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር ለመንገዶች አስተዳደር ለከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ ለኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፣ ለመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር፣

ለኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት፣ ለኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን፣ ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ለቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና ለባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የበጀት ድጋፍ ጭማሪ ተደርጓል።

የ2017 በጀት ዓመት የካፒታል ወጪ

በቢሊዮን ብር

አገልግሎት	የ2016 የጸደቀ በጀት	የ2017 በጀት		ልዩነት		ድርሻ በመቶኛ
		የተጠየቀ	የተደገፈ	በመጠን	በ%	
1	2	3	4	5=4-2	6=5/2	
አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት	31.41	68.49	43.34	11.93	37.98	15.30
ኢኮኖሚ	129.29	185.47	163.73	34.44	26.64	57.81
ማህበራዊ	37.24	82.36	65.91	28.67	76.99	23.27
ሌሎች	5.50	9.22	10.22	4.72	85.82	3.61
ድምር	203.44	345.54	283.20	79.76	39.21	100.00



6.2.2.1 ከካፒታል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው

የ2017 በጀት አመት የካፒታል ወጪው ሲዘጋጅና ድጋፍ ሲሰጥ ዘላቂ ልማት የማምጣት፣ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንን የማረጋገጥ እና ድህነትን የማስወገድ ዕቅድን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ከካፒታል ወጪው ውስጥ ከፍተኛ ትኩረትና የበጀት መጠን ያላቸው የሥራ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው::

- በመሠረተ ልማት በኩል የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ለዋና መንገዶች፣ ለአገናኝ መንገዶች ግንባታ እና ነባሮቹን ለማጠናከርና ለማሻሻል ለተጀመሩ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 75.0 ቢሊዮን ተደግፏል:: በአጠቃላይ ለመንገድ ፕሮጀክቶች የውጭ ፋይናንስን ጨምሮ ብር 85.0 ቢሊዮን የተደገፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለዋና መንገዶች ማጠናከርና ማሻሻል ብር 21.8

ቢሊዮን፣ ለአዲስ መንገዶች ግንባታ ብር 56.7 ቢሊዮን እና ለመንገዶች ከባድ ጥገና ብር 2.75 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- ለከፍተኛ ትምህርት ነባር ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከመንግሥት ግምጃ ቤት ብር 33.0 ቢሊዮን እና ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 200.0 ሚሊዮን እንዲሁም ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፖኬጅ የውጭ ፋይናንስ ጨምሮ ብር 610.9 ሚሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት ለነባርና ለትላልቅ መስኖዎች ግንባታ ብር 10.1 ቢሊዮን እንዲሁም በቆላማ አካባቢዎች የቴክኖሎጂ ስርፀት በማድረግ የአካባቢውን ህብረተሰቡ ኑሮ ለማሻሻል ብር 1.0 ቢሊዮን በካፒታል በጀት ተደግፎ ቀርቧል፡፡ ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ የመካከለኛና የትናንሽ መስኖዎች ግንባታ በቀጥታ በክልሎች በኩል ለመተግበር በዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ ስር ብር 8.0 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ ንብረቶች እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ለማድረግ ለመልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 20.0 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡

- የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽንን በተመለከተ ብር 9.3 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 2.31 ቢሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎችን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ለሚሟላት የተደገፈ ነው፡፡


- የግብርናውን ዘርፍ በመስኖ ልማት ለመደገፍ በአነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ለሚካሄድ የተቀናጀ አነስተኛ የመስኖ ልማት ኘሮጀክት በልዩ ሁኔታ ብር 600.0 ሚሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- በገጠር የስራ ዕድልና የምግብ ዋስትና ጋር ለተገናኘው ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 7.3 ቢሊዮን እና ከውጭ ፋይናንስ ብር 3.7 ቢሊዮን በድምሩ ብር 11.0 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡ በተመሳሳይ ለከተማ ምግብ ዋስትናና ልማታዊ ሴፍቲኔት ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 3.2 ቢሊዮን እና ከውጭ ፋይናንስ ብር 9.1 ቢሊዮን በድምሩ ብር 12.3 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡

- ለጤና ሴክተር ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 8.7 ቢሊዮን እና ከውጭ ፋይናንስ ብር 15.3 ቢሊዮን በድምሩ ብር 24.0 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- የመንግስት አገልግሎቶችን በተመቻቸ ቦታ ለመስጠትና የቢሮ ኪራይ ለመቀነስ እንዲቻል ለመንግሥት ቢሮዎች ግንባታ ፕሮጀክት ብር 5.2 ቢሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፎ ቀርቧል፡፡

ከዚህ በላይ የተሰጡት ማብራሪያዎች በዋና ዋና ወጪዎች ላይ ያተኮሩ ሲሆን በአስፈጻሚ መ/ቤቶችና በበጀት ዓይነት በመለየት በጥራዝ ሁለት የበጀት ሠነድ ውስጥ በዝርዝር መግለጫ ተሰጥቶበታል፡፡



6.2.3. ከፌዴራል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው

ከዚህ በላይ በፌዴራል የመደበኛና የካፒታል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን ለማሳየት ተሞክሯል። ከዚህ ቀጥሎ የመደበኛና የካፒታል ወጪ ተዳምረው ሲታይ የክፍላተ ኢኮኖሚ ድርሻ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ከአጠቃላይ ከፌዴራል በጀቱ ከብር 734.51 ቢሊዮን ውስጥ 34.6 በመቶ ድርሻ ያላቸው መንገድ፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ውሀና ኤነርጂ፣ ግብርና እና የከተማ ልማት ናቸው። ይህም ከ2016 በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር የበጀት ድርሻው ጭማሪ ያላሳየው ለኢንዱስትሪ ፖርኮች ልማት ኮርፖሬሽን፣ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ለኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ድጋፍ በጀት በመያዙ ነው። በፌዴራል ደረጃ የግብርና፣ የጤና እና የውሃ ሴክተር በጀት ድርሻ ከሌሎች አነስተኛ ሆኖ ቢታይም በአብዛኛው ስራዎቹ በክልሎች የሚካሄዱ በመሆኑ የእነዚህ ሴክተሮች የበጀት ድርሻ የክልሎችን ሲጨምር በሀገር ደረጃ ከፍተኛ እንደሚሆን ይገመታል።

በተጨማሪም የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንና ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ትርጉም ላላቸው የማኑፋክቸሪንግ፣ ኤክስፖርትና የከተማ ልማት ዘርፎች ከፍ ያለ በጀት መመደቡን ከሠንጠረዡ መገንዘብ ይቻላል። በአጠቃላይ ከፌዴራል በጀቱ ውስጥ የዕዳ ክፍያ 18.97 በመቶ፣ መንገድ 11.73 በመቶ እና ትምህርት 10.87 በመቶ ድርሻ አላቸው።

በፌዴራል የመደበኛና ካፒታል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው

በቢሊዮን ብር

ተ.ቁ	ዋና ዋና ወጪዎች	መጠን	%
1	ዕዳ ክፍያ	139.31	18.97
2	መንገድ	86.00	11.71
3	ትምህርት	79.84	10.87
4	መከላከያ	65.70	8.94
5	ጤና	33.90	4.62
6	ፍትህና ደሕንነት	27.64	3.76
7	ውሀ ሀብትና ኤነርጂ	25.26	3.44
8	ግብርና	22.92	3.12
9	አደጋ መከላከል	11.90	1.62
10	ትራንስፖርት እና መገናኛ	11.89	1.62
11	ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም	6.57	0.89
14	የከተማ ልማት	5.98	0.81
15	ሌሎች	217.60	29.63
	ድምር	734.51	100.00

7. የወጪ አሸፋፈን

በ2017 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ከሀገር ውስጥ የገቢ ምንጮች እና ከውጭ ዕርዳታ በድምሩ ብር 612.7 ቢሊዮን እንደሚሰበሰብ ተገምቷል። ከዚሁ ውስጥ ከአገር ውስጥ ገቢ ብር 563.6 ቢሊዮን፣ በቀጥታ በጀት ድጋፍ ከሚገኝ ከመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ዕርዳታ ብር 7.3 ቢሊዮን እና ከፕሮጀክቶች ዕርዳታ ብር 41.8 ቢሊዮን ሊገኝ እንደሚችል ታቅዷል።

በሌላ በኩል ለፌዴራል መንግሥት የመደበኛ ወጪ 451.3 ቢሊዮን (46.5%)፣ የካፒታል ወጪ ብር 283.2 ቢሊዮን (29.2%)፣ ለክልሎች ድጋፍ ብር 222.7 ቢሊዮን (22.9%) እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14.0 ቢሊዮን (1.4%) በድምሩ ብር 971.2 ቢሊዮን ወጪ ታቅዷል። በዚህም መሠረት በገቢው 612.7 ብር ቢሊዮን እና በጠቅላላ ወጪው ብር 971.2 ቢሊዮን መካከል የብር 358.50 ቢሊዮን የበጀት ጉድለት ይታያል።


የዚህ የበጀት ጉድለት ብር 358.5 ቢሊዮን የፋይናንስ ምንጭም በቀጥታ በጀት ድጋፍ ከሚገኝ ከመሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ብድር ብር 0.6 ቢሊዮን፣ ከፕሮጀክት ብድር ብር 32.3 ቢሊዮን እና ከሀገር ውስጥ ብድር ብር 325.6 ቢሊዮን ለመሸፈን ታቅዷል። ከጠቅላለ የበጀት ጉድለት ውስጥ ብር 49.7 ቢሊዮን ለመንግስት ዋና እዳ ክፍያ የሚውል ነው። በመሆኑም የተጣራ የበጀት ጉድለት ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ያለው ድርሻ 2.06% ሲሆን የተጣራ የሀገር ውስጥ ብድር ድርሻ ደግሞ 2.15% በመሆኑ የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ተግባራዊ ከሚደረገው የገንዘብ ፖሊሲ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ ስለሆነ በዋጋ ንረት ላይ ተጽእኖ እንደማያሳድር ይታመናል። ዝርዝሩ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥና ሥዕላዊ መግለጫ ተመልክቷል።



የ2017 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የገቢና ወጪ

ዕቅድ ማጠቃለያ (በቢሊዮን ብር)

I. ጠቅላላ ገቢ		**612.7**
1.1 ታክስ ገቢ	502.04	
1.2 ታክስ ያልሆኑ	60.39	
1.3 መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ዕርዳታ	7.30	
1.4 ፕሮጀክት ዕርዳታ	41.79	
1.5 የካፒታል ገቢ	1.18	
II. ጠቅላላ ወጪ		**971.2**
2.1. መደበኛ ወጪ	451.31	
2.2. ካፒታል ወጪ	283.20	
2.3 የክልሎች ድጋፍ	222.69	
2.4. ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ	14.00	
III. የበጀት ጉድለት (I – II)		**-358.5**
የውጭ ሀገር ብድር		**32.92**
3.1 መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ብድር	0.60	
3.2. ፕሮጀክት ብድር	32.32	
የሀገር ውስጥ ብድር		**325.58**
3.3. የሀገር ውስጥ ብድር	325.58	


የ2017 በጀት አመት የፌዴራል መንግስት ገቢ ፣ የውጭ ዕርዳታና ብድር /በቢሊዮን ብር/
የአገር ውስጥ ገቢ, 563.6, 58.0%
መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ዕርዳታ 7.3, 0.75%
መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ብድር 0.6, 0.06 %,
ፕሮጀክት ብድር 32.3, 3.3 %,
ፕሮጀክት ዕርዳታ 41.8, 4.3 %,
የሀገር ውስጥ ብድር, 325.6, 33.5 %,